# ኢፕድ አዲስ ዘመን

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 160 የካቲት 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# «አፍሪካ ቀጣይነት ያለው ልማትን ለማረጋገጥ የዲጂታል ሽግግርን ማፋጠን አለባት»

**- ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ**



**ጌትነት ምሕረቴ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ ሁሉን አቀፍና ቀጣይነት ያለው ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የዲጂታል ሽግግርን ማፋጠን እንደሚኖርባት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ገለፁ።

ከአፍሪካ ኅብረት 37ኛው የመሪዎች ጉባዔ ጎን ለጎን ለአፍሪካ ሁለተናዊ ለውጥ ዲጂታል ቴክኖሎጂን መታጠቅ በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት የአፍሪካ የተቋማት መሪዎች በተገኙበት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ፓንአፍሪካ አዳራሽ ውይይት ተካሂዷል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በዚህ ወቅት እንዳሉት፤ አፍሪካ ከፍተኛ የተፈጥሮና የሰው ኃይል እምቅ አቅም አላት፡፡ ይህን አቅም በመጠቀም ዘላቂ ልማትና ዕድገት ለማምጣት የዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር ማፋጠን ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ እየታየ ያለው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ፈጣን ዕድገት በአፍሪካ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካ፣ ባህልና ማኅበረሰብ ላይ ጉልህ ተጽእኖ እየፈጠረ መሆኑን አመልክተው፥ ዲጂታላይዜሽንን ማፋጠን

«አፍሪካ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሀገር ዕድገትና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ትምህርት ቁልፍ ሚና ይጫወታል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የሀገር ዕድገትና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ትምህርት ቁልፍ ሚና ይጫወታል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡


37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ «ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን አፍሪካዊ ማስተማር፤ የማይበገሩ የትምህርት ሥርዓቶች በመገንባት በአፍሪካ ሁሉን አቀፍ፣ የሕይወት ዘመን፣ ጥራትና አግባብነት ያለው የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት» በሚል መሪ ሃሳብ እየተካሄደ ነው።

በ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ በሀገር ዕድገትንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ

የሀገር ዕድገት...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ- ሓዱሽ አብርሃ



# የበለፀገች አፍሪካን እውን ለማድረግ ኅብረቱ እና አባል ሀገራት ጠንክረው ሊሠሩ ይገባል

**- የሞሪታኒያው ፕሬዚዳንት የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበርነትን ተረክበዋል**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የበለፀገች አፍሪካን እውን ለማድረግ ኅብረቱ እና አባል ሀገራት ጠንክረው ሊሠሩ ይገባል ሲሉ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ መሃመት ገልጸዋል። የሞሪታኒያው ፕሬዚዳንት የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበርነትን ተረክበዋል፡፡

37ኛው የአፍሪካ ኅብረት መደበኛ የመሪዎች ጉባኤ

የበለፀገች አፍሪካን...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ኢፕድ ለአዲሱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይፋዊ አቀባበል፤ ለቀድሞው ሽኝት አደረገ

ገጽ 4














ዜና

# በክልሉ 10 ሚሊዮን የአቮካዶ ችግኝ እየተዘጋጀ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ለክልሉ የፍራፍሬ ልማት የሚውል 10 ሚሊዮን የአቮካዶ ችግኝ እየተዘጋጀ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ አንድ ሺህ ቶን የአቮካዶ ምርት ወደውጭ ገበያ ለመላክ መታቀዱም ተገልጿል፡፡

የቢሮው ምክትል ኃላፊና የቡናና ፍራፍሬ ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሐመድሳኒ አሚን ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በተለያዩ ጣቢያዎች እየተዘጋጀ የሚገኘው የአቮካዶ ችግኝ እንደየአካባቢው የአየር ንብረት ተለይቶ ይተከላል።

የአቮካዶና ፍራፍሬ ልማቱ ዋነኛ የልማት ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ አርሶአደሩ ችግኞቹን ተቀብሎ በማልማት ውጤታማ የሚሆንበትን አሠራር እየተላመደ መሆኑን ተናግረዋል።

የማሳ ሽፋን የማስፋፋት ሥራ ባለፈው ዓመት መጀመሩን አስታውሰው፤ በ2015 በጀት ዓመት 16 ሄክታር መሬት ላይ የአቮካዶ ችግኝ የተተከለ ሲሆን በዘንድሮ ዓመት 25 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል 10 ሚሊዮን ችግኝ እየተዘጋጀ መሆኑን አስረድተዋል።

ዘንድሮ የሚተከለውን የአቮካዶ ችግኝ ጨምሮ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ አጠቃላይ የክልሉ የአቮካዶ ማሳ ሽፋን ከ40 ሄክታር በላይ እንደሚደርስ አስረድተዋል፡፡

አቶ መሐመድ እንደተናገሩት፤ በባለፈው በጀት ዓመት በሦስት ዙር 180 ቶን የአቮካዶ ምርት ወደውጭ ገበያ በመላክ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

ባለፈው ዓመት የተተከለው አቮካዶ ዘንድሮ ፍሬ እያፈራ እንደሚገኝ በመግለጽ፤ በክልሉ በተያዘው በጀት ዓመት አንድ ሺህ ቶን ምርት ለውጭ ገበያ ለመላክ ታቅዷል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ምክትል ኃላፊው ገለጻ፤ ከክልሉ የአቮካዶ ምርት በዋናነት ወደ ስፔን፣ ዱባይ፣ ሳውዲ ዐረቢያ እየተላከ የሚገኝ ሲሆን፤ ከተለያዩ የአውሮፓ ሀገራትም ጥያቄ እየቀረበ ያለበት ሁኔታ ቢኖርም ሥራው ገና ጅማሮ ላይ ያለ በመሆኑ የምርት እጥረት አለ፡፡

አሁን ላይ አቮካዶ ወደውጭ የሚልክ በምሥራቅ ሸዋ የሚገኝ አንድ ማኅበር ብቻ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ በጅማ ዞንና በሌሎች አካባቢዎች ላኪዎችን ለማስፋፋት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

አቮካዶ ቶሎ የሚበላሽ የምርት ዓይነት እንደመሆኑ የምርት ማከማቻ አለመኖርና የሌሎች መሠረተ ልማቶች እጥረቶች ይበልጥ ለገበያ ለማቅረብ ተግዳሮት መሆኑን አንስተዋል፡፡

ከወደብም ጋር ተያይዞ ችግር መኖሩን ያነሱት አቶ መሐመድ ፤ ከክልሉ ተነስቶ እስከ ጂቡቲ ድረስ ምርቱ ተጭኖ ሲሄድ ወጪው ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከወደብ ጋር ያለውን ችግር ከሱማሌ ላንድ ጋር የተያዘው ስምምነት ተስፋ የሚሰጥ እንደሆነ በመግለጽ፤ ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት በመንግሥት በኩል የሚሠሩ ሥራዎች የሚደገፉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

# 9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም እየተካሄደ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ ከትናንትና ጀምሮ እየተካሄደ ነው፡፡

«የዘመኑ ከተሞች ለኢትዮጵያ ብልፅግና» በሚል መሪ ሃሳብ እየተካሄደ የሚገኘው 9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ከትናንት ጀምሮ ለተከታታይ ሰባት ቀናት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ሶዶ ከተማ ነው የሚካሄደው።



ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ 9ኛው የከተሞች ፎረምን በይፋ በከፈቱበት ወቅት እንደተናገሩት፤ መንግሥት ከሀገራዊ ለውጡ በኋላ ከተሞችን የማልማትና የማስዋብ እንዲሁም ትልልቅ የቱሪስት መዳረሻዎች ግንባታን ማከናወኑን ገልጸዋል።

ሀገራችን በለውጥ ጎዳና ላይ ትገኛለች ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዘርፎች የተመዘገቡ ለውጦችን ጠቅሰዋል።

በለውጡ ሂደት በርካታ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሙም ፈተናዎችን በመሻገር የብልፅግና ጉዟችንን እናረጋግጣለን ብለዋል።

የከተሞች መልማትና መስፋፋት የሕዝቦችን ትስስርና ኅብረብሔራዊነትን ያጎለብታል ያሉት አቶ ተመስገን፤ በኢትዮጵያ ከለውጡ ወዲህ መንግሥት ባከናወናቸው በርካታ የልማት ተግባራት ተጨባጭ ለውጥ መምጣቱን ተናግረዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር፤ ፎረሙ ከተሞች ስኬቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበትና የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት መሆኑን ገልጸዋል።

ይህንንም በመጠቀም ከተሞችን ለተሻለ ብልፅግና ማሻገር እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

የዘንድሮ ከተሞች ፎረም ከፌዴራል ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥትና የወላይታ ዞን አስተዳደር በጋራ በመሆን የተዘጋጀ ነው።

ከየካቲት 9 እስከ 15 ቀን 2016 ዓ.ም በሚካሄደው በዚህ ፎረም 125 ከተሞች ተመዝግበዋል፡፡ በተረከቡት ቦታም እራሳቸውን የሚያስተዋውቁ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ከ50 በላይ የንግድ ድርጅቶችና የተለያዩ ተቋማት ይሳተፋሉ።

በከተሞች ተሞክሮ ዙሪያ አውደ ጥናት እና ኤግዚቢሽን ጨምሮ ከተሞች እርስ በርስ ትብብር እና አብሮነታቸውን በሚያጠናክሩባቸው ጉዳዮች ላይ የሚመክሩ ይሆናል።

የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ከተሞች ስኬቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበት፤ ተሞክሮ የሚለዋወጡበት እና ተግባር ተኮር የምርምር ግኝቶች የሚቀርቡበት መድረክ ነው።

በሥነ - ሥርዓቱ ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣ የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒን ጨምሮ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ጥላሁን ከበደ እንዲሁም ሌሎች የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# ሀገራዊ ምክክሩ ቅድሚያ በሰላም ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሠራ ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩ ቅድሚያ በሰላም ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ቢወያይ የተሻለ እንደሚሆን አስተያየታቸውን ለኢፕድ የሰጡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገለፁ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ፍቅረወርቅ የሺጥላ እንደተናገሩት፤ ሀገራዊ ምክክሩ በዘላቂነት ውጤት እንዲያመጣ በቅድሚያ በሀገሪቱ በሚስተዋሉ ችግሮችና በሰላም ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል።

መረጋጋት በሌለባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች መወያየት የሚችሉበትን ዕድል ለመፍጠር፤ ሀገራዊ ምክክሩ በቅድሚያ በግጭት ውስጥ ያሉ አካላት የሚነጋገሩበትንና ጥያቄያቸውን በሰላማዊ መንገድ የሚያቀርቡበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል ሲሉ አስረድተዋል።

የሁሉም ጥያቄ የሚፈታው በጦርነት ሳይሆን በውይይት ነው ያሉት ወይዘሮ ፍቅረወርቅ፤ ነፍጥ ያነሱ አካላትም ጥያቄያቸውን አቅርበው ለውይይት ዕድል ሊሰጡ ይገባል ብለዋል፡፡

ነዋሪዋ እንደተናገሩት፤ ሀገራዊ ምክክሩ ከዚህ በፊት ያልነበረ እንደመሆኑ አሁን ላይ ደንብ ተቀርጾለት ወደትግበራ መግባቱ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

በዚህም ሁሉም ክልሎችና የሀገሪቱ ነዋሪዎች ጥያቄያቸውን ለውይይት እንዲያቀርቡ ዕድል የሚፈጥርና ችግር የሚፈታ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያውያን አንድላይ ወደፊት ለመራመድ የቀረበላቸውን አማራጭ ሊጠቀሙ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሌላኛዋ የአዲስ አበባ ነዋሪ ትግስት ተስፋዬ በበኩሏ፤ የሀገራዊ ምክክሩን የመጨረሻ ውጤት መልካም ሆኖ ማየት እንዲቻል፤ በቅድሚያ ሰላም ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ተደርጎ በሰላም ላይ ውይይት ሊደረግ ይገባል ብላለች፡፡



ወይዘሮ ፍቅረወርቅ የሺጥላ፤



ትግስት ተስፋዬ፤

ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ እና በሪሁን ታደሰ

ሀገሪቱ አሁን ካለችበት ሁኔታ አንጻር ምክክሩ በሰላም ላይ የተሻለ አጀንዳ ቀርጾ ከላይ እስከታች ውይይት ሊደረግ እንደሚገባ አመላክታለች።

ነዋሪዋ እንደተናገረችው፤ ለሁሉም ነገር ሰላም ትልቅ ነገር እንደመሆኑ በቅድሚያ በሰላም ጉዳይ ላይ አጀንዳ ቀርጾ መወያየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል በልማትና በሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ መድረኮችን ማስፋት ይገባል።

ስለምክክሩ በፍጥነት የተረዱና ዘግይተው መረጃ የሚደርሳቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ስላሉ በተለያየ ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች፤ ምሁራንና የሃይማኖት አባቶች ስለሰላም አጀንዳ ለማኅበረሰቡ በስፋት ማስረዳትና ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ይበልጥ መሥራት ይኖርባቸዋል ብላለች።

በሀገራዊ ምክክሩ ላይ የሚሳተፉ አካላት ከማኅበረሰቡ የተሻለ ዕውቀት፤ በቂ ሥነ-ምግባርና አመለካከት ይኖራቸዋል ተብሎ ይታመናል ያለችው ነዋሪዋ፤ ይህም በየአካባቢው የሚፈጠሩ አሉባልታዎችንና ግጭቶችን በዘላቂነት ለመቅረፍ ይረዳል ስትል አስረድታለች፡፡

የሀገራዊ ምክክሩ መድረኮች ሲጀመሩ በሀገሪቱ በሚፈጠሩ የሰላም ጉዳዮች ላይ ቅድሚያ በተለያዩ ምሁራንና የማኅበረሰብ ተወካዮች በየዘርፉ ውይይት ተደርጎበት መድረስ ቢችል እንዲሁም በተዋረድ ጉዳዩ ለማኅበረሰቡ እንዲደርስ ማድረግ ይገባል ስትልም አስተያየቷ ሰጥታለች።

በመጨረሻም የሀገራችንን የሰላም እና የልማት ጉዳይ ለሌሎች የምንገፋው ጉዳይ ስላልሆነ፤ ሁሉም ዜጋ በእኔነት ስሜት እና በአወንታዊ ሃሳብ ከላይ እስከታች ሊሳተፍ ይገባል ስትል ሃሳቧን ሰጥታለች፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ እና ፓን አፍሪካኒዝም- ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት እስከ አፍሪካ ኅብረት!

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ቀደምት፣ የመንግሥት ሥርዓቷም ያልተቋራረጠ ሀገረ መንግሥት ባለቤት ናት። ይሄ የቀደምትነትና ያልተቆራረጠ ሥርዓተ መንግሥት ባለቤትነቷ ደግሞ ነፃ እና ጠንካራ ሆና እንድትዘልቅ አድርጓታል። ይሄ ነፃነትና ጥንካሬዋ ደግሞ ከራሷ አልፋ ለአፍሪካ፣ ከአፍሪካም ከፍ ብላ ለመላው የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ምልክት እንድትሆን አስችሏታል፡፡

በተለይ ኢትዮጵያ እንደ አንድ ነፃ እና በቅኝ ያልተገዛች ሀገር ብሎም እንደ አንድ አፍሪካዊት ሀገር፣ ለአፍሪካውያን ነፃነትና ሉዓላዊነት ከፍ ያለ ዋጋ ከፍላለች። በዚህም አፍሪካውያን ከቅኝ ተገዥነት በተግባርም በአሳቤም ነፃ እንዲወጡ የሚያስችላቸውን የፓን አፍሪካኒዝም አሳቤ በመያዝ፣ አፍሪካውያን በአንድ ተሰባስበው ለነፃነትና ሉዓላዊነታቸው እንዲታገሉ በማድረግ ገረድ ከፍ ያለ ሚናን ተወጥታለች፡፡

ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ሕብረት) እውን መሆን ከፍ ያለና እልህ አስጨራሽ ዲፕሎማሲያዊ ሥራን ሠርታለች። ለዚህ ደግሞ የነፃነት ምድር መሆኗ ትልቅ ሚና የነበረው ሲሆን፣ በወቅቱ የነበሩ መሪዎችና ዲፕሎማቶቿም ሚናቸው ጉልህ ነበር፡፡

ይሄ ጥረቷም፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እውን ያደረገ ሲሆን፣ አፍሪካውያንም በአንድ መድረክ ተሰባስበው ለነፃነትና ብልጽግናቸው በጋራ እንዲሠሩ፣ ነፃነታቸውንም እንዲጎናጸፉ አስችሏል። በኋላም ለአፍሪካ ኅብረት መመስረት መንገድ አደላድሏል፣ ኢትዮጵያም በተቋሙ ታግዛ ለአፍሪካውያን ነፃነት የድርሻዋን እንድትወጣ አቅም ፈጥሮላታል፡፡

ይህ እንዲሆን ጥንስሱ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውን መሆን ነው። ይሁን እንጂ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የመመስረት ሂደቱ ቀላል አልነበረም። ይልቁንም አፍሪካውያን በቅኝ ገዥዎቻቸው በተፈጠረባቸው የባህል ተጽዕኖ ምክንያት ርስ በርሳቸው በቋንቋ ሳይቀር ተከፋፍለው ነበር። ኢትዮጵያም በወቅቱ መሪዋ በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት አመራር ታግዛ ይሄንን ለማስታረቅ ከፍ ያለ የዲፕሎማሲ ሥራን ከውና በተለይ የካዛብላንካ እና የሞኖሮቪያ ቡድኖችን ለማቀራረብ ችላለች፡፡

ይሄም በአህጉሪቱ ታሪክ አንድነትን፣ ልማትን፣ ሰላምን እና ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እጅግ መሠረታዊ የሆነ ታሪካዊ ምዕራፍ ሲሆን፣ በወቅቱም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት በኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ ውስጥ በወርቃማ ፓን-አፍሪካዊ ቀለም የተፃፈ የዲፕሎማሲ ዘመን ሆኖም ይታወሳል።

በወቅቱ ከመለያየት ይልቅ አንድነትን የመረጡ 32 አባል ሀገራት በተገኙበት ግንቦት 1963 ዓ.ም የመሪዎቹ ስብሰባ በአዲስ አበባ ተጀመረ። በወቅቱም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የስብሰባው ሊቀመንበር እንዲሆኑ በሙሉ ድምፅ ተመረጡ። ከቀናት ምክክር በኋላም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር በመሪዎች ተፈርሞ «አህጉሩን ከቅኝ እና ከአፓርታይድ አገዛዞች ፈጽሞ ማላቀቅ፣ በአፍሪካ ሀገራት መካከል አንድነትን እና ወዳጅነትን ማጠናከር፣ ለልማት የሚደረገውን ትብብር ማጠናከር፣ የአባል ሀገራትን ሉአላዊነት እና የግዛት አንድነት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ትብብር ማጠናከር፣» የሚሉ ዓላማዎችን ይዞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተመሰረተ።

የድርጅቱን እውን መሆን ተከትሎም፣ አፍሪካውያን ጉዳዮቻቸውና ችግሮቻቸው ከእነሱ ውጪ በሆኑ አካላት ይታይ የነበረበት አካሄድ መታረም እንዳለበት አቅጣጫ ተቀመጠ። አፍሪካውያን የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው መክረው የመፍታት አቅምም መብትም እንዳላቸው በግልጽ ተቀመጠ። «ከጥቂት ዓመታት በፊት የአፍሪካ ችግሮች ከአፍሪካ ውጪ አፍሪካውያን ባልሆኑ ወገኖች ውሳኔ ይሰጠበት ነበር፣ ዛሬ አፍሪካውያን ጉዳያቸውን በራሳቸው የሚመክሩበት ዕድል በዚህ ኮንፈረንስ ተፈጥሯል፡፡" የሚለው የወቅቱ የአፄ ኃ/ሥላሴ ንግግርም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነበር፡፡

በዚህ መልኩ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ሂደት የታየው የኢትዮጵያ ሚና፣ በኋላም አፍሪካውያን በዓለም መድረክ ተሰሚነትና ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው እንዲጨምር የሚያስችሉ በርካታ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ስትከውን ቆይታለች። በኋላም ድርጅቱ ወደ ሕብረት (የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወደ አፍሪካ ኅብረት) ሲለወጥ የድርሻዋን የተወጣች፣ የኅብረቱ ልዕልና እንዲጠበቅም የተጋች ሀገር ናት፡፡

ለአብነትም፣ ኅብረቱ አፍሪካዊ ተቋም ሆኖ እንዲገለጽ ከሚያስችሉት ጉዳዮች መካከል አንዱ ፋይናንስ ነው። ይሄን የፋይናንስ ፍላጎቱን ለማሟላት ደግሞ አባል ሀገራቱ መዋጮ አንዱ መንገድ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ የኅብረቱን መዋጮ ከሚያዋጡ በጣት ከሚቆጠሩ ሀገራት ቀዳሚዋ ናት። በተመሳሳይ ኅብረቱ በዓለም መድረኮችና ዓለምአቀፍ ተቋማት ቋሚ ውክልና እና ድምጽ እንዲኖረው ለማስቻል ያልተቋራረጠ ሥራ እየሠራች ትገኛለች፡፡

በዚህ ሁሉ ጉዞ ከውስጧ ባላወጣችው የፓን አፍሪካኒዝም አሳቤ መሰረትም፣ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም የአፍሪካ ጉዳዮችና ችግሮች በራሳቸው አፍሪካውያን እንዲሁም የራሳቸው ተቋም በሆነው የአፍሪካ ኅብረት አቅምና ዐውድ ውስጥ ሆነው መታየትና መፈታት እንዳለባቸው አጽንዖት ሰጥታ እየሰራችም ነው። አፍሪካውያን ነጻነታቸው ምሉዕ ሆኖ እንዲገለጽ የማኅበራዊ መሰረታቸው እንዲጠናከር፣ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው እንዲጎለብት፣ የመሰረተ ልማት ትስስራቸው በጋራ ተጠቃሚነትና አብሮ በመበልጸግ መርህ እንዲቃኝ አበክራ እየለፋች ያለች ናት። ይሄው አሳቤና ጥረቷ ከትናንትን የቀጠለ፣ ዛሬም ያለ፣ ወደፊትም የሚዘልቅ ስለመሆኑም የታመነ ነው!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አፍሪካውያን ትልልቅ አእምሮዎችን ማክበር እና ማወደስ አለብን!

ሚሊዮን ሺበሺ

አፍሪካውያን በቀደሙት ዘመናትም ሆነ አሁን ከፍ ያለ የሃሳብ ልዕልና ያላቸው መሪዎችን ማፍራት ችለዋል። እነዚህ መሪዎች ከፍ ያሉ ሃሳቦችን በማንሳት ለአህጉሪቱ እና ለሕዝቦቿ ብሩህ ነገዎችን ለመፍጠር በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሰዋል። ሕይወታቸውን የጠየቀ መስዋእትነትም ከፍለዋል። ለእነዚህ መሪዎች ተገቢውን ክብር መስጠት ስላልተቻለ ዛሬም አፍሪካ የባለ አእምሮ ችግር ያለባት አህጉር አድርገው የሚገምቱ ጥቂት አይደሉም።

በተለይም የምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን በስፋት አፍሪካንና ሕዝቦቿን ከሚያዩበትና ከሚዘግቡበት የተጣመመ (የተዛባ) ትርክት አንጻር፣ ዓለምአቀፉ ኅብረተሰብ ስለ አህጉሪቱ ያለው እሳቤ በእጅጉ የተሳሳተ ነው። ይህ ደግሞ በአህጉሪቱ ዛሬዎች ላይ እየፈጠረ ያለው ሁለንተናዊ ተጽእኖ ቀላል አይደለም።

በአብዛኛው የምዕራቡ ዓለም የመገናኛ ብዙኃን የሚሠሯቸው ዘጋቢ ፊልሞች የአፍሪካ መሪዎችን አስተሳሰብ ከፍታ ሳይሆን ክፋትና ዘራፊነት ... ወዘተ ነው። ከዚህ አልፈው ትውልዶችን ማሻገር የሚያስችሉ አፍሪካውያን ጥልቅ አእምሮዎች መናገር እና እነሱን ማወደስ አይፈልጉም።

እንደ አጼ ምኒልክ ያሉ የታላቅ ሕዝብ ታላቅ መሪ፣ እንደ ኩዋሜ ኒኩሩማ ያሉ የነፃነት ታጋዮችን፣ እንደ ጁሊየስ ኒሬሬ ያሉ ዴሞክራት መሪዎችን፣ እንደ አጼ ኃይለሥላሴ ያሉ የአህጉሪቷን አባቶችን ... ወዘተ አንስተው ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ለመናገርና ለማሳወቅ ድፍረቱ የላቸውም።

ይህ ዛሬ ላይ ጭምር ያልተሻገርነው አፍሪካዊ ችግራችን በዋንኛነት እኛን የሚመለከት ስለመሆኑ ለመናገር የሚከብድ አይደለም። እኛ አክብረን ከፍ ያላደረግናቸውን አእምሮዎቻችንን ሌሎች እንዲያከብሩዋቸው፣ በአደባባይ እንዲያወድሷቸው መጠበቅ የዋህነት፣ ከዚያም በላይ ከእኛ አንጻር ቂልነት ነው።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለብንን ክፍተት ማየት ሳይሆን ክፍተቱን ለመሙላት መሞከር ነው፣ ለዚህም ሳምንቱ የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ የሚካሄድበት መሆኑን እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ የኅብረቱ መሥራች እና የነፃነት ታጋይ የነበሩ የአፍሪካ መሪዎችን እናስታውስ፣ እናወድስ።

የአፍሪካ መሪዎች የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የመሠረቱት ብዙ የውስጥ እና የውጭ ጫናዎችን ተቋቁመው ነው። በዚህ የመሰባሰብ ሂደት ኢትዮጵያ እንደ አንድ ነፃ መንግሥትና ሕዝብ፣ ከዚያም ባለፈ ዘመናት ያስቆጠረ የሀገረ መንግሥት ትርክት ባለቤት በመሆን፣ ያበረከተችው አስተዋጥኦ በኅብረቱ ምስረታ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው።

የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኅብረቱን ለመመስረት በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። አሁን ላለው አፍሪካዊ ትውልድ ባለ ውለታ ስለመሆናቸውም የታሪክ ተመራማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መፈጠሩ በራሱ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ለተረዳው ማረጋገጫ የሚጠይቅ አይደለም።

የዛየር (ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ) መሪ የነበረው ፓትሪስ ሉሙምባ ያሉ የነፃነት ታጋዮች አፍርታለች። ሉሙምባ ለዛየራውያን ጥልቅ ህልም አልሞ በህልሙ ምክንያት ለሞት የተዳረገ አፍሪካዊ ባለ ጥልቅ አእምሮ ነው። ይህን ተጨባጭ እውነታ ከመናገር ይልቅ አፍሪካውያን ሳይቀር መናገር የሚፈልጉት የሚቀናቸውም፣ የዛየር አምባገነን መሪ ስለነበረው ሞቡቱ ሴሴ ሴኮ ነው፡፡

በእርግጥ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች አምባገነኖች ናቸው። ሥልጣን የሚለቁት በተፈጥሮ ኃይል ወይም በመፈንቅለ መንግሥት ነው። ዳሩ ግን አፍሪካ ለዓለም አርዓያ የሚሆን ሥራ የሠሩ እና የሚመሰገኑ መሪዎችም አሏት። ለዚህም፣ የታንዛኒያ መሪ የነበሩት ጁሊየስ ኒሬሬ ሥልጣን የለቀቁት በራሳቸው ፈቃድ ነው።

ከ32 የአፍሪካ አንድነት መሥራቾች አንዱ የነበሩት የካሜሮኑ መሪ አህማዶ አህዲጆ «አሁን ያለሁበት የጤና ሁኔታ ሀገር ለመምራት የሚያስችል አይደለም» በማለት በራሳቸው ፈቃድ ሥልጣን የለቀቁ ናቸው። በተመሳሳይ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራቾች አንዱ የነበሩት የሱዳኑ መሪ ኢብራሂም ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቀዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የነዚህ አፍሪካውያን ታሪክ አይታወቅም።

**በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዓለም የሥልጣኔ እና የዴሞክራሲ ቁንጮ ናት የምትባለው አሜሪካ ብዙ የምርጫ ማጭበርበር ሲወራባት፤ የአፍሪካዊቷ ሀገር ታንዛኒያ መሪ ጁሊየስ ኒሬሬ ግን በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሥልጣን በራሳቸው ፈቃድ ለቀው ለዓለም ምሳሌ ሆነዋል**

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዓለም የሥልጣኔ እና የዴሞክራሲ ቁንጮ ናት የምትባለው አሜሪካ ብዙ የምርጫ ማጭበርበር ሲወራባት፣ የአፍሪካዊቷ ሀገር ታንዛኒያ መሪ ጁሊየስ ኒሬሬ ግን በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሥልጣን በራሳቸው ፈቃድ ለቀው ለዓለም ምሳሌ ሆነዋል። ሆኖም ግን አፍሪካ ውስጥ የሚደረግን በጎ ነገር ማመስገን የማይቀናቸው የምዕራባውያን መገናኛ ብዙኃኖች፣ ጁሊየስ ኒሬሬን ለማመስገን ቃል አላገኙም።

ከዚያ ይልቅ ዘጋርዲያን ጨምሮ አብዛኞቹ የምዕራባውያን ጋዜጦች በክስተቱ ዙሪያ ከሠሯቸው ዘገባዎች፣ ኒሬሬ በሀገሩ ሕዝብ የማይወደድ፣ ሶሻሊዝምን አሰርጻለሁ ብሎ ሀገሩን ድህነት ላይ የጣለ አድርገው ነው። እውነታው ግን ከዚህ በተጻራሪ ኒሬሬን የሀገሩ ሕዝብ «ሙዋሊሙ» እያለ ይጠራው እንደነበር ነው።

ሙዋሊሙ ማለት በእስዋሂሊ «መምህራችን፣ አባታችን» እንደማለት ነው። «ዴሞክራሲ በራስህ ሀገር ዓውድ የምታዳብረው እንጂ እንደ ኮካ ኮላ ከውጭ የምትገዛው አይደለም» በሚለው ንግግሩ የሚታወቀው ኒሬሬ ፣ ሶሻሊዝምን እንደ ወረደ መቀበል ሳይሆን ከታንዛኒያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ያደረገ አፍሪካዊ ባለ ትልቅ አእምሮ፣ በሀገሩ ሕዝብም ምስጋና የሚቸረው ነው።

እነ ኔልሰን ማንደላ፣ ኩዋሜ ኒኩሩማህ፣ ጆሞ ኬንያታ፣ ሴዳር ሴንጉር፣ ኬኔት ካውንዳ የመሳሰሉት የአፍሪካ መሪዎች የውጭ ወራሪን በመታገል ለአፍሪካ ሀገራት ነፃነት ውለታ የዋሉ ናቸው። እንደነ ሳሞራ ማሼል፣ ሮበርት ሙጋቤ የመሳሰሉት በአገዛዛቸው «አምባ ገነን» የነበሩ ቢሆንም ሀገራቸውን ከውጭ ብዝበዛ ነፃ ለማድረግ ሲጋፈጡና ሲታገሉ የነበሩ ናቸው።

እንደነ ቶማስ ሳንካራ የመሳሰሉት «አፍሪካዊ ቼ ጉቬራ» የሚል ቅጽል ስም የተሰጣቸው አብዮተኞችንም አፍሪካ አፍርታለች። እነዚህን ማስታወስ፣ ሃሳባቸውንና ከዚህ ለመነጨው ሥራቸው እውቅና መስጠት፣ ማክበርና ማወደስ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነው። የራሱን ጀግኖች ለማወደስ አቅም የማይኖረው ትውልድ ራሱን ጀግና ያፈራል ብሎ ማሰብ «ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደሚባለው» ከመሆን ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም ።

# ኢፕድ ለአዲሱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይፋዊ አቀባበል፤ ለቀድሞው ሽኝት አደረገ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ቢሾፍቱ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለቀድሞ የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሽኝት፤ ለአዲሱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ደግሞ አቀባበል አደረገ፡፡ ኢፕድ የሠራተኞች ዓመታዊ በዓሉን በቢሾፍቱ ከተማ ትናንት አክብሯል።

የቀድሞ የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የኢፕድ ሠራተኞች አመራሩ የሚሠጣቸውን አቅጣጫ ተቀብለው በብቃት የሚወጡ ናቸው፡፡ ለዚህም ተቋሙ በገቢ፣ በይዘት፣ በሌሎች ሚዲያዎች ያለው ተጠቃሽነት እና በተቋሙ የተሠሩት የሪፎርም ሥራዎች ማሳያ ናቸው ብለዋል።

አሁን ላይ ኢፕድ ከሌሎች የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ጋር ተወዳዳሪ ነው ያሉት አቶ ጌትነት፤ ለዚህ ውጤት የተቋሙ ቦርድ፣ አመራሮች እና ሠራተኞች ሚና እንደሆነ ተናግረዋል።

አሁንም እንደተቋም የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ከአዲሱ ሥራ አስፈፃሚ ጋር በትብብር መሥራት ይገባል በማለት ለአዲሱ የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መሳፍንት ተፈራ መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆን ተመኝተዋል።

በመጨረሻም በተቋሙ ሠራተኞችና በቦርድ አባላት ለተበረከተላቸው ስጦታ አመስግነዋል።

የኢፕድ የቦርድ አባል ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በበኩላቸው፤ ኢፕድ በታሪካዊ ቦታና እጥፋት ላይ ነው። ወደፊት የኢፕድ ሕንፃ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስና ትምህርት በሚገለፅበት ቦታ ላይ ይሆናል። በዚህም የኢፕድ ዐሻራ ሙዚየም አንዱ መሆኑን ገልፀዋል።

ይህ ቦታ የትናንቱን ከዛሬ ጋር ከማገናኘት ባለፈ የቱሪዝም መዳረሻ ይሆናል። ትልቅ ለውጥ እየመጣ ነው። በዚህም ሠራተኛው፣ አመራሩ፣ የምክር ቤትና የቦርድ ሰፊ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ዶክተር ካይረዲን ተዘራ በበኩላቸው፤ የኢፕድ ቦርድ አባል ከነበርኩበት ጊዜ አንስቶ በተቋሙ በርካታ ለውጦች ተመዝግበዋል። ኢፕድ ዜናዎችን በኦንላይን እና በጋዜጣ ተደራሽ ከማድረግ በላይ ሀገራዊ የሆኑ የውይይት መድረኮችን አዘጋጅቷል። ይህንንም አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

በተለይ እንደ ስለኢትዮጵያ ያሉ የኢፕድ ብራንዶች ማጠናከር ይገባል ብለዋል።



ወይዘሮ ነብያ መሐመድ በበኩላቸው፤ ሚዲያ ኃይል ነው። ትንሽ ሕዝብ ኖሯቸው በሚዲያዎቻቸው ጠንካራ ሥራ የሠሩ በርካታ ሀገራት አሉ። ስለዚህ ኢፕድ የተደራሽነት፣ የይዘት እና ሀገራዊ ጉዳዮችን በመያዝና በማጠናከር ለኢትዮጵያ ገፅታና ደጀን ለመሆን መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

የቀድሞ የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ ተቋሙን ገንብተዋል። አቶ መሳፍንት ደግሞ ይህንን እንደሚያሳድጉና እንደሚያጠናክሩ አምናለሁ ብለዋል።

በኢፕድ ቦርድ ሆኜ ሳገለግል ለ2ተኛ ጊዜ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የቦርድ ስብሰባ ላይ 43 ጥያቄዎች ቀርበዋል። ይህንን ለመፍታት ተቸግረን በነበረበት ወቅት አቶ ጌትነት ታደሰ ችግሮቹን ለመፍታት ጠንካራ ሥራዎችን ሠርተው ለውጥ ማምጣታቸውን የተናገሩት ደግሞ ረዳት ፕሮፌሰር መኩሪያ መካሻ ናቸው።

በመርሐ ግብሩ የተቋሙ የ6 ወር አፈፃፀም ለቦርድ አባላትና ሠራተኞች የቀረበ ሲሆን፣ በዚህም በለውጥ ላይ ያለውን ተቋም በአዳዲስ ፈጠራና መንገድ ወደ ተሻለ ከፍታ የሚያሸጋግሩ ሥራዎችን መሥራት እንደሚገባ ተገልጿል።

በመርሐ ግብሩ ላይ በተቋሙ የተለያዩ የፕሮጀክት ሥራዎች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የድርጅቱ አመራርና ሠራተኞች እውቅና ተሰጥቷል።

በበዓሉ ለቀድሞ የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ ሽኝት የተደረገ ሲሆን፤ ተቋሙ እና ሠራተኞች አቶ ጌትነት ለነበራቸው መልካም የሥራ አስተዋጽኦ አመስግነው ስጦታ አበርክተውላቸዋል።

በተመሳሳይም ለአዲሱ የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መሳፍንት ተፈራ የሥራ አመራር ቦርዱ አመራሮችና ሠራተኞች በይፋ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

# «አፍሪካ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ጫናዎችን ለመቋቋምና ለችግሮች ፈጣን መፍትሔ ለመስጠት አመቺ እንደሆነ ተናግረዋል።

አጀንዳ 2063ን ለማሳካትና የበለፀገች አፍሪካን ለመፍጠር የዲጂታላይዜሽን መስፋፋትና መጠቀም ጉልህ ሚና እንደሚኖረው የተናገሩት ፕሬዚዳንቷ፤ ኢትዮጵያም ከአህጉሪቱ ዕሳቤዎች ጋር የሚጣጣም ዲጂታል 2025 ስትራቴጂ በማዘጋጀት ወደ ሥራ መግባቷን ጠቅሰዋል።

በዚህም የቴሌኮም መሠረተ ልማትን በሰፊው በመገንባት፣ የሞባይልና የኢንተርኔት ተደራሽነት በማስፋፋትና አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዙሪያ ላይ ተጨባጭ ተግባራት እያከናወነች መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በተለይ በፋይናንስ፣ በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በአገልግሎት አሰጣጥና በጸጥታ ዘርፎች ሁሉን አቀፍ የዲጂታል ኢኮኖሚ እየገነባች እንደምትገኝ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ገልጸው፤ በእነዚህ ሴክተሮች በስፋት በመጠቀም ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እየተጋች ነው ብለዋል።

መጪው ዘመን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ኢትዮጵያ ይህን ታሳቢ አድርጋ ሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚ ለመገንባት በትኩረት እየሠራች መሆኑን አንስተዋል። በተለይ በቴሌኮም ዘርፍ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ሲሆን ተጠባቂ ውጤቶችም እየተመዘገቡ መሆኑን አብራርተዋል።

በሁሉም ሴክተሮች ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣትም አሁንም አህጉሪቷ የቴሌኮም መሠረተ ልማት ግንባታና በሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ላይ ትኩረት አድርጋ መሥራት እንደሚጠበቅባት ነው ያስታወቁት፡

ዲጂታል ቴክኖሎጂ የአህጉሪቷን ዘላቂ ዕድገትና ሁለንተናዊ ለውጥ ለማረጋገጥ እንደሚያስችል ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ገልጸው፤ ይህን ዕውን ለማድረግም ዕውቀት መር ዲጂታላይዜሽን ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራት አለበት ብለዋል፡፡

በተለይ ሰው ሠራሽ አስተውሎትና በዳታ አጠቃቀም ዙሪያ ላይ ቅድሚያ ተሰጥቶ መሠራት እንደሚኖርበት አመልክተው፤ ለዚህም የትምህርት ፖሊሲውን ማሻሻልና ሥርዓተ ትምህርቱን መከለስ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ዲጂታል ሽግግርን በማፋጠን ምርታማነት ማሳደግ፣ የሥራ ዕድልን መፍጠር፣ ፈጠራን ማስፋፋትና ሁሉን አቀፍ የፋይናንስ ተደራሽነትን ማረጋገጥና ቀጣናዊ ትብብርን ማጠናከር ቀጣይ የቤት ሥራዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በውይይቱ የአፍሪካ ሀገራት የፋይናንስ መሪዎች እንዲሁም የቴሌኮም ሴክተር የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

# የበለፀገች አፍሪካን እውን ለማድረግ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በኅብረቱ ዋና መቀመጫ አዲስ አበባ ትናንት ተጀምሯል፡፡

በ37ኛው የኅብረቱ ጉባዔ መክፈቻ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽነር ሙሳ ፋኪ መሃመት ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ አፍሪካ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚገባትን ቦታ እንድታገኝ ኅብረቱ እና አባል ሀገራት ጠንክረው ሊሠሩ ይገባል፡፡

የበለጸገች አፍሪካን እውን ለማድረግ በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ አካታችና ዘላቂ ልማት ግቦች ማሳካት እንደሚገባ ገልጸው፤ እቅዱን በማሳካት አፍሪካን ጠንካራ፣ ሰላማዊ እና የበለፀገች እንድትሆን ሁሉም አካላት እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

የአጀንዳ 2063 አንዱ ግብ አህጉሪቱን የሰላም ቀጣና ማድረግ ቢሆንም በአህጉሪቱ አንዳንድ ሀገራት በሚፈጠሩ ግጭቶች በርካቶች ለሕልፈትና ለሰብዓዊ ቀውስ እየተዳረጉ መሆኑን አንስተዋል።

በየጊዜው እየተበራከቱ የመጡት መፈንቅለ መንግሥታት እና በታጠቁ ኃይሎች የሚደረጉ ግጭቶች አህጉሪቱ ወደ ፊት እንዳትሄድ እያደረጋት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሱዳን፣ በምዕራብ አፍሪካ ሀገራት እና ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እየተፈጠሩ ያሉ ቀውሶች ለአብነት አንስተው፣ አህጉሪቱን ከነዚህ ችግሮች ማላቀቅ ካልቻልን የምንመኛትን አፍሪካ እውን ለማድረግ ያዳግታል ብለዋል፡፡

የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች እና ኅብረቱ ችግሩን በመፍታት ለአጀንዳ 2063 ስኬት የሚበጁ የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው አስታውቀዋል፡፡

ኅብረቱ በአጀንዳ 2063 ያቀዳቸው እቅዶች አብዛኛዎቹ ያልተሳኩ መሆናቸውን ገልጸው፤ በዚሁ ከቀጠለ ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ እንደሚሆን አስረድተዋል፡፡

አጀንዳ 2063 የአፍሪካ ኅብረትን ማጠናከር ሌላኛው ግብ በመሆኑ ለኅብረቱ ሀብት የማሰባሰብ ፕሮግራም ዳር እንዲደርስ፣ ኢንቨስትመንት እና ፋይናንስ አቅም እንዲጎለብት መምከር እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል የሞሪታኒያው ፕሬዚዳንት መሐመድ አውልድ ኤል ጋዞኒ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበርነትን ከኮሞሮሱ ፕሬዚዳንት አዛሊ አሶማኒ ተረክበዋል።

የበለፀገች አፍሪካን እውን ለማድረግ በትምህርት ዘርፍ ሀገራቱ በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባ የወቅቱ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀመንበር ሞሃመድ አውልድ ኤል ጋዞኒ ገልጸዋል።

የበለፀገች አፍሪካን እውን ለማድረግ እና የአጀንዳ 2063ን ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ዜጎችን በማስተማር ተወዳዳሪና ብቁ ለማድረግ በቁርጠኝነት መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ የወቅቱ ሊቀመንበር ሞሃመድ አውልድ ኤል ጋዞኒ ተናግረዋል፡፡

በአህጉሪቱ 62 በመቶው ወጣት መሆኑን ገልጸው፤ ወጣቱን በማስተማርና በማሠልጠን የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ የሁሉም ሀገራት ኃላፊነት ነው ብለዋል፡፡

አፍሪካን በመሠረተ-ልማት የማስተሳሰር ተግባራት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በዚህም የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና በማጠናከር አህጉሪቱን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

በአህጉሪቱ ስጋት የሆነው የሰላም እጦትንና ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት አፍሪካውያን ቁጭ ብለው በመነጋገርና በዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ችግሮችን በራስ አቅም መፍታት የሚያስችል ስልት ሊከተሉ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የአየር ንብረት ለውጥ ፈተናን መጋፈጥ የሚያስችል ቁመናን መገንባትም የየሀገራቱ የቤት ሥራ መሆን እንደሚገባው ሊቀመንበሩ አሳስበዋል።

# የሀገር ዕድገትና ዘላቂ ልማትን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ትምህርት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት በትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ዕድገትና ለውጥ ማሳየቷን የገለጹት ዶክተር ዐቢይ 30 ሺህ ሙዓለ ሕፃናት እንዲሁም የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመገንባትና በማሻሻል ለውጥ አምጥታለች ብለዋል፡፡

የሰው ሠራሽ አስተውሎት ራስን በራስ ለማስተማር እንደሚረዳ ጠቅሰው፤ በተለይም የባህልና የቋንቋ ተግዳሮቶችን በመሻገር ሕፃናትን በትምህርት ለማነጽ እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

በአዳዲስ ቴክኖሎጂና ፈጠራ የታገዘ ጉዞ አፍሪካን ወደ ቀጣዩ የዕድገት ምዕራፍ ያሸጋግራታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ቴክኖሎጂ የትምህርት አሰጣጡን ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን አስችሏል ብለዋል፡፡

አፍሪካ ምቹ የአየር ፀባይ፣ የሚታረስ መሬት፣ ውሃ፣ ደን፣ የተፈጥሮ ሀብትና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት የሰው ኃይል እንዳላት ጠቅሰው፤ በጂኦ ፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ የአየር ንብረት ለውጥና በቴክኖሎጂ መራቀቅ ሳትበገር በተሻለ የዕድገት ጎዳና በመራመድ ላይ እንደምትገኝ ገልጸዋል፡፡

አፍሪካ በዓለም የኃይልና ኢኮኖሚ አሰላለፍ ውስጥ ቁልፍ ሚናዋን እንድትወጣ በጋራ መሥራት አለብን ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ አፍሪካ ሰፊ መሬት፣ እምቅ የተፈጥሮ ሀብትና በርካታ የወጣት ኃይል እያላት ተረጂ ልትሆን አይገባም ብለዋል።

የአፍሪካ ሕዝብ በ2050 ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን በመሆን በሕዝብ ብዛት ቀዳሚ አህጉር እንደምትሆን ጠቅሰው፤ በዓለም አቀፉ የገንዘብ ሥርዓት ውስጥ ያለው አለመመጣጠን አዳጋች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአፍሪካ መሠረተ ልማትን መገንባት፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ጤናን ጨምሮ የትምህርት ሥርዓትንና የሥራ ዕድል ፈጠራን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ ይህን እውን ለማድረግ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት በትኩረት ሊያዩት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በአፍሪካ በርካታ የአፍሪካ ሕዝቦች ተንቀሳቃሽ ስልክ ያላቸው በመሆኑ ዲጂታል ኢኮኖሚ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚፈልገውን ከፍተኛ የዳታ ማዕከል ግንባታ መጀመሯን ገልጸዋል።

የፓን አፍሪካ የዳታ ማዕከል መገንባት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የአህጉሪቱንና የግለሰቦችን የዳታ ዝውውር በማፋጠን ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እንደሚያስችል አመላክተዋል፡፡

በሀገራት የመንገድ፣ የአየር፣ የንግድ፣ የወደብ፣ የባቡርን ጨምሮ የነዳጅ ማስተላለፊያና የኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ትስስር ጠቃሚ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሠረት የሆኑትን ሰላምና መረጋጋት ማስፈን አለብን ብለዋል፡፡

በ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ የተገኙት የብራዚል ፕሬዚዳንት ሉላ ዳ ሲልቫ በበኩላቸው፤ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ያለው ኢ-ፍትሐዊ አሠራር በአስቸኳይ ሊፈታ ይገባዋል፡፡

እንደ ዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ የብድር አሠራር ተበዳሪ ሀገራትን በሚለውጥ መልኩ መሆን እንዳለበት ጠቅሰው፤ አፍሪካ በሌሎችም ዓለም አቀፍ ተቋማት ያላት ውክልና ጫና ውስጥ የከተታት ነው ብለዋል፡፡

ለአፍሪካ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ አፋጣኝ ጥረቶች እንደሚያስፈልግ በመግለጽ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማትን ከመፍጠር አንፃር ብራዚል ከአፍሪካውያን ጎን እንደምትቆም አረጋግጠዋል።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የምንሻት ታላቋ አፍሪካ የምትፈጠረው በታላቅ ሀሳብና ተግባር ነው

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)**

የአፍሪካ ሕብረት እ.ኤ.አ በ1963 መገባደጃ ላይ 32 በሚሆኑ የወቅቱ የአፍሪካ ነጻ መንግስታት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በሚል ስያሜ ተመሰረተ። ከአራት አስርት ዓመታት በኋላ ደግሞ የአሁኑን መጠሪያ ሊይዝ ቻለ። እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2002 የመጀመሪያውን የመሪዎች ጉባኤ ሲያካሂድ ቀድሞ ይዞት ከመጣው ዓላማና ተልዕኮ ጋር የተዋሃደ ተጨማሪ አፍሪካዊ ጉዳዮችን አጀንዳው አድርጎ ቀጥሏል። የ2063 አሁጉራዊ አጀንዳም የዚሁ አካል ነው፡፡

በዘንድሮው የሕብረቱ ጉባኤ ላይም በዋናነት ሰላምና ደህንነት፣ ቀጠናዊ ጥምረትና እድገት መወያያ አጀንዳ ሆኖ ከፊት ተቀምጧል።ሰላምና ደህንነት የወቅቱ አኅጉራዊ ጉዳይ ከመሆኑ አንጻር አጀንዳ መሆኑ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። በዚህ ዙሪያ ገና ያልተወጧቸው የቤት ስራዎች በርካታ ናቸው፡፡

እነዚህ አጀንዳዎች በቀደሙት የሕብረቱ የመሪዎች ጉባኤ ቀርበው ውይይት ቢደረግባቸውም ችግሩ ለዘለቄታው ሊፈታ አልቻለም። በሰላምና ጸጥታ ጉዳች ሕብረቱ ተወያይቶ አቅጣጫ አስቀምጦ መፍትሄ ያላመጣባቸው አስረጂዎች እዚም እዛም አሉ፡፡

ሕብረቱ እንደ ድርጅት ሲቋቋም የመጀመሪያ ዓላማው የአፍሪካውያንን ነፃነት በማረጋገጥ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊ ተጠቃሚነት ማጽናት ነው። በተለይም ፀረ ቅኝ ግዛት ትግሉ በድል ከተጠናቀቀ በኋላ፤ ኢኮኖሚያዊ ነጻነትን ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አቅጣጭ ይዞ መንቀሳቀስ ቆይቷል። እስካሁን ባለው ሁኔታ ብዙ ለውጦች ማስመዝገብ ቢችልም የተጠበቀውን ያህል ግን መሄድ አልቻለም።

እንደሚታወቀው አፍሪካ ብዙ የተፈጥሮ ጸጋዎች ባለቤት ብትሆንም አሁንም ይህንን ሀብት ወደሚፈለገው ብልጽግና ለውጣ ለነዋሪዎቿ ለኑሮ የተሻለች ማድረግ አልተቻለም። ከነበረችበትና ካለችበት የኢኮኖሚ ጥገኝነት መላቀቅ አልተቻለም። ይህን ዘመናት አብሮን አየተጓዘ ያለ ችግር ለመለወጥ ከሁሉም በላይ የአፍሪካ ሕብረት ትልቅ አቅም እንደሚሆን ይታመናል።

አፍሪካውያን ባላቸው አቅም የራሳቸውን እድል በራሳቸው እንዲወስኑ ከሁሉም በላይ ቁርጠኝነትን የሚፈልጉ እና የአብሮነት ትስስርን የሚሹ በውይይትና በምክክር የሚፈቱ በርካታ የጋራ ጉዳዮች አሏቸው።በራስ መተማመን ላይ የተመሰረተ ማንነት ከመፍጠር ጀምሮ ስለሰላምና ስለለውጥ ቁጭ ብለው በሰከነ መንፈስ የሚነጋገሩባቸው መድረኮች ያስፈልጓቸዋል፡፡

አፍሪካ ከትላንት እስከዛሬ ሌሎች ባደረሱባት ሰንኮፍ ስር ናት። ይሄን ሰንኮፍ አውልቃ በራሷ መልክና ደም ግባት፣ ችሎታና ጽናት፣ ኢኮኖሚና መርህ፣ ፖሊሲና እቅድ መቆም አለባት።ይሄ እንዲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ቁርጠኝነት የታከለበት የመሪዎች ውይይትና ውሳኔ ነው።

ቁርጠኝነት በሌለበት ሁኔታ የተደጋገሙ ውይይቶች እና የአቋም መግለጫዎች በራሳቸው የሚያመጡት ነገር አይኖርም። ወቅቱ በበረታ የሀሳብ ሙግት የበረታች አፍሪካን ለመፍጠር ወገብ ማጥበቅ የሚፈለግበት ነው።በተግባር መር አስተሳሰብ ነገሮችን በኃላፊነት መንፈስ ተቀብሎ እና ዋጋ ከፍሎ መራመድን የሚጠይቅ ነው።

**ቁርጠኝነት በሌለበት ሁኔታ የተደጋገሙ ውይይቶች እና የአቋም መግለጫዎች በራሳቸው የሚያመጡት ነገር አይኖርም**

ቅኝ ግዛት ካሉት ብዙ መልኮች አንጽር፤ አሁን ላይ በአፍሪካ ምድር እየሆነ ያለው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አፍሪካን እና አፍሪካውያንን ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ነው። በእርዳታ ስም የሚገቡ እጅ መጠምዘዞች፣ እከክልኝ ልከክልህ አይነት አሳቤዎች የዚህ የቅኝ ግዛት መልኮች አንድ መገለጫዎች ናቸው።

አፍሪካውያን አሁን ላይ በኢኮኖሚው ሆነ በፖለቲካው መስክ ለሚያደርጓቸው የለውጥ ንቅናቄዎች የሌሎችን ፍቃድ ማግኘት ግድ የሚልበት ዘመን ላይ ደርሰዋል። ይህን ተጽእኖ ተቋቁሞ ለመሻገር አፍሪካውን አንድነታቸውን አጥብቀው ከመሄድ ባለፈ ሊኖራቸው የሚችለው ሌላኛው አማራጭ ብዙም አስተማማኝ አይደለም።

የአፍሪካ ሕብረት ይህንን ሕብረት ለመፍጠር አደራ የተጣለበት ትልቅ አህጉራዊ ተቋም ነው። በዚህም የአህጉሪቱን፣ የሕዝቦቿን ፖለቲካዊ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ በአፍሪካ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ መግለጫዎችን አውጥቶ ከመለያየት ባለፈ የሚጨበጥ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ተግባራዊ እርምጃ ይጠበቅበታል።

በዚህ ዓለም እድገትና ስልጣኔን ለማምጣት ዋነኛ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል፤ የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ኃይል ተጠቃሽ ናቸው።እንደ እድል ሆኖ ሁለቱም በአፍሪካ ምድር የሚገኙ ናቸው። ይህም ሆኖ ግን በእስካሁኑ አፍሪካውያን በተፈጥሮ ጸጋቸው ሌሎችን ከመጥቀም ባለፈ ራሳቸውን ሲጠቅሙ አይታይም። አሁንን ድንነትና ኋላቀርነት ውስጥ ናቸው።

ይህ ጉዳይ መቋጫ እንዲያገኝ የአፍሪካውያን ፍላጎት ነው።መጪውን ጊዜ በብስለትና በንቃት ቃኝተን ከራሳችን ለራሳችን በሆነ መሪ ሀሳብ ከድህነትና ከተረጂነት የምንወጣበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ የአፍሪካ ሕብረት የሚኖረው አስተዋፆ መተኪያ የሌለው እንደሚሆን ይታመናል።

እኛ ያቃተን የራሳችንን ሀብት በራሳችን እውቀት መጠቀም ነው። ይህ የሆነው በእውቀት ችግር ስላለብን ብቻ ሳይሆን ከሁሉም በላይ ሀብቶቻችንን አልምተን እንዳንጠየቀም ያለው የውጪ ጣልቃ ገብነት ነው። ይህንን ጣልቃ ገብነት ለማስቆም በጋራ መሰረት ላይ የቆመ ትግል አለማድረጋችን ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል አያደረገን ነው።

ይህ ለዓመታት የመጣንበት መንገድ እንዲያበቃ፤ ከሴራ ፖለቲካ፤ እርሱ ከሚፈጥረው የእርስ በርስ ጦርነት እና ግጭት መውጣት አለብን። በድህነት፣ በኋላ ቀርነት መውጣት የሚያስችለንን አንድነት አቅም መገንባት ይኖርብናል። በተፈጥሮ ሀብቱ የበይ ተመልካች የሆነውን የአህጉሪቱን ሕዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ስለ አንድነት መትጋት ይጠበቅብናል።

ከመጀመሪያው የሰው ዘር አፈጣጠር ጀምሮ አዲስ ነገር ያለው አፍሪካ ውስጥ ነው።ሌሎች ሀገራት ለዘመናት ሲሰጡን የነበረው ከእኛው የወሰዱትን ነው። ባለን ልክ አጠቃቀም አልቻልንም። ካለፈው በመማር መጪዋን አፍሪካ መታደግ ከሁላችን የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

አፍሪካ ራሷን ችላ መቆም አለባት። የአፍሪካ ሕብረት ደግሞ በአንድነቱና በምክረ ሀሳቡ አፍሪካ የምትነሳበትን መላና መፍትሄ መፍጠር ለነገ የማይለው የቤት ስራው ነው። በአፍሪካ ጉዳይ ላይ ወደ ኋላ የማይሉ አዲስ አስተሳሰቦችን፣ አዲስ ትውልዶችን ማፍራት ይጠበቅበታል። በአህጉሪቱ ጉዳይ ላይ የማይናወጥ አቋም መገንባት በይደር የማይተው አበይት ጉዳዩ ሆኖ ከዛሬ ወደነገ መሄድ አለበት፡፡

አፍሪካ ራሷን መፍጠር፣ ታሪኳን እንደ አዲስ መጻፍ፣ በቤቷና በርስቷ ላይ ዳግማዊ ወረራን መፍቀድ የለባትም። ለምንድነው የምንከሽፈው? ተነጋግረን ተወያይተን ለውጥ የማናመጣው ለምንድነው? የአፍሪካ ሕብረት አፍሪካን ከስቃይ መታደግ ያልቻለው ለምንድነው? መግደልና መሞት በዋጀው በአንድ አይነት ርዮተ ዓለም ስለምን? እኒህ ጥያቄዎች መልስ ይፈልጋሉ።

ጥያቄዎቹ በፍጥነት መልስ ሊያገኙ ይገባል። የአፍሪካን ችግሮች በዘላቂነት መቅረፍ የሚቻለው ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ መስጠት ሲቻል ነው። ተጠቃሚነታችን ለሌሎች አሳልፈን መስጠት አይኖርብንም። እጣ ፈንታችን ከእኛው በእኛው ለእኛ ሆኖ እንዲቀጥል አፍሪካ ሕብረት ከመቼውም ጊዜ በላይ በርትቶ መስራት ይኖርበታል።

አህጉሩን ከዘመናዊ ባርነት ለመታደግ፣ ከኢኮኖሚና ከመሰል ጥገኝነት ተላቆ ራስን በቻለ ፖለቲካና የአመራር ክህሎት ወደፊት ለማስቀጠል የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን በሚል እሳቤ መንቀሳቀስ አንዱና ዋነኛው የመፍትሄ ሀሳብ ነው። የአፍሪካ የነጻነት ትንሳኤ ያለው በአፍሪካውያን ትብብር ውስጥ ነው።

የሕዝቦቿ ተጠቃሚነት የተቀመጠው በሕዝቦቿ አንድነት ውስጥ ነው። ራሳችንንም ታሪካችንንም ከጣልቃገብነት ለመጠበቅ የትብብር መንፈስን መላበስ ይኖርብናል። «የአንተ ቤት ሲንኳኳ እኔ ቤት ይሰማል..» እንደሚባለው፤ የአንዱን ሕመም አንዱ በመታመም ራሳችንን ነጻ ማውጣት አለብን።

የትብብር መንፈስ የማይፈጥረው ተዓምር የለም። የአንድነት መንፈስ ልክ እንደ አድዋ ሁሉ አሁንም በአፍሪካ ላይ ጣልቃ ገብነትን የሚሽር ነው።መልስ የሚፈልጉ ብዙ አፍሪካዊ ጥያቄዎች ቢኖሩም የነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መነሻ ማዕከል ግን አንድነት ነው። በተለይ አሁን ላለንበት ቀጠናዊና አህጉራዊ ተግዳሮት ሕብረት የወለደው አንድነት ግድ የሚልበት ሰሞን ላይ ነን።

የችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ ውይይት ነው። አፍሪካ አንድ ስትሆን ችግሮቻችን አቅም አይኖራቸውም። የተሸነፍነው ችግሮቻችንን በራሳችን መፍታት አቅቶን ለሌሎች አሳልፈን በመስጠታችን ነው። የተረታነው በመነጋገር ወደሰላም ከመምጣት ይልቅ ጦርነትን የመፍትሄ አካል አድርገን ስለተቀበልን ነው። በኢትዮጵያ የነጻነት ተጋድሎ መላውን አፍሪካ ከባርነት ማውጣት ከተቻለ በመላው አፍሪካ አንድነትና ሕብረት ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡

አሁንም በጅምር የቆሙ ነጻነቶቻችንን በእጃችን ማስገባት ይኖርብናል። የተሟላ ነጻነት ያስፈልገናል... ገና ከምንፈልገው የነጻነት ጥግ አልደረስንም።ካለ ማንም ርዳታና እገዛ በራሳችን የምንቆምበት ጊዜ፣ በራሳችን እውቀትና ጥበብ ወደ ፊት የምንራመድበት ጊዜ ይናፍቀናል።ይሄ ሁሉ እንዲሆን ፖለቲካና ኢኮኖሚያችንን ለራሳቸው እንዲመች አድርገው ልንሰራው ይገባናል፡፡

አፍሪካውያን ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የሚተርፉ በርካታ ልጆች አሏቸው። መያያዝና መቀራረብ ከቻልን የማንፈታው የችግር ቋጠሮ አይኖርም። የአፍሪካ ሕብረት በሀገራት መካከል የአንድነትና የትብብር መንፈስን በመጓዝ በአጭር ጊዜ የምንናፍቃት አፍሪካ ተፈጥራ ማየት የምንችልበትን እድል መፍጠር ይችላል።

የሕብረቱ መሪዎች በምክረ ሀሳባቸው የአፍሪካ ሕዝባችን የጋራ መሻት እውን ለማድረግ ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ መንቀቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። የምንፈልጋት ታላቋ አፍሪካ የምትፈጠረው በታላቅ ሀሳብና በታላቅ ተግባር ውስጥ ነው።ይሄ እንዲሆን ታላቅ አቅም የሚፈጥር የወዳጅነት መንፈስን ከሁሉ አስቀድመን እንላበስ። ሰላም!

# የሕይወት ገጽታ

## በማሳጅና በወጌሻነት ለብዙዎች ፈውስ የሆነች -ልበ ብርሃን ሴት

**እፀገነት አክሊሉ**

ሕይወት መልከ ብዙ ናት።ለአንዱ ብትመች ለሌላው ጎዶሎ ጎኗ ሊበዛ ይችላል ።ግን ደግሞ ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ ሞላለትም ጎደለበትም ኑሮ ይሉትን ገመድ መጎተቱ አይቀሬ ነው።በዚህ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ደግሞ አካል ጉዳተኝነት ሲታከልበት ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን መገመቱ አያስቸግርም።አካል ጉዳተኝነት በራሱ ይዞት የሚመጣው ሰፊ የጤና ችግር ከመኖሩም ባሻገር ሰዎች እንደ ልባቸው ተንቀሳቅሶ መስራት ካለመቻል ጋር ተደማምሮ ችግሩ ብዙ ነው።

አካል ጉዳተኝነት በማንኛውም ጊዜና አጋጣሚ በሁሉም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ችግሩ መከሰቱን አምኖ ሕይወትን በጥንካሬ መግፋት ለውጤት እንደሚያበቃ ብዙዎች ምስክር ናቸው፡፡

አንዳንዶች ብዙ መስራት በሚችሉበት እድሜያቸው ላይ ሆነው በሚያጋጥማቸው ቀላልም ሆነ ከባድ የአካል ጉዳት ምክንያት ቤት ለመዋል፤ ተስፋ ለመቁረጥ፤ ከእኩዮቻቸው በታች የመሆን አልፎ ተርፎም በቤተሰብና በአገር ላይ ተጨማሪ ሸክም ለመሆን ይገደዳሉ። ሌሎች ደግሞ የደረሰባቸውን ጉዳት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምና በማመን በተሰጣቸው ልክ ሰርተው ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የጠቀሙ በርካቶች መሆናቸውን ማንሳት ይቻላል።

ለዛሬ የሕይወት ገጽታ አምዳችን እንግዳ ያደረግናት ወጣትም ለብዙ ወጣት አካል ጉዳተኞች ተምሳሌት የምትሆን ብርቱ፣ ራዕይ ያላት፤ ጉዳቷን ይዛ ቤት ውላ የሌሎችን እርጥባን ከመጠበቅ በራሷ ተንቀሳቅሳ የምትኖር ለተቸገሩ ሰዎች መፍትሔ የሆነች ናት።

ወጣት ብሌን ሰለሞን ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ መካኒሳ አካባቢ ነው።ለእናቷ ብቸኛ ልጅ የሆነችው ብሌን በጥሩ እንክብካቤ ነበር ያደገችው።ኋላም እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን ትከታታል ዘንድ በእናቷ አማካይነት መሰረተ ኢትዮጵያ ትምህርት ቤት ገባች።

ብሌን ከእኩዮቿ ጋር እየተማረች፤ እየተጫወተች በጠቅላላው አንድ ታዳጊ ሕጻን ሊያደርገው የሚገባውን ሁሉ እያደረገች በተለይም እናቷ እየተደሰቱባትና ነጋቸውን በእሷ ውስጥ እያዩ ሶስተኛ ክፍል ደረሰች።ከዚህ በኋላ ግን ብሌን ሕይወቷን ወዳልታሰበ መንገድ የቀየረ መጥፎ አጋጣሚ ወደእሷና ቤተሰቧ ጎራ አለ።



**ብሌን በማሳጅ ስራዋ የነርቭ፣ የኩላሊት፣የልብ የስኳርና የደም ግፊት፣ እንዲሁም አስምና ሳይነስ ሕመሞችን ለማስታገስ የሚጠቅሙ የማሳጅ አይነቶችን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን በመነካካትና በማሸት ታስታግሳለች**

“.......እናቴ ብቸኛ ልጇም ስለሆንኩ በጥሩ እንክብካቤ ነው ያሳደገችኝ ፡፡ የምፈልገውን አሟልታ ከሰው እንዳላንስ አድርጋ ትምህርት ቤት አስገብታ ብቻ በጠቅላላው ከእናት የሚጠበቀውን ሁሉ አድርጋና ጎዶሎዬን ሞልታ ነው ያሳደገችኝ።ትምህርት ቤትም ከገባሁ በኋላ ጥሩ የትምህርት አቀባበል ነበረኝ” ትላለች።

ብሌን የሶስተኛ ክፍል ትምህርቷን እየተማረች ሳለች በአንዲት መጥፎ ቀን ከመምህሯ ጋር ትጋጫለች። በዛ በለጋ እድሜዋ ያጠፋችው ጥፋትና የተወሰደባት የቅጣት እርምጃ ግን ፍጹም ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ብሌንን ለዘላላም የአካል ጉዳት ዳረጋት።

ልጆች በትምህርት ቤት ሊያጠፉ ሊሳሳቱ አልፎ ተርፎም ሊረብሹ ይችላሉ። ከቤተሰብ ቀጥሎ ያሉት የቅርብ ቤተሰቦቻቸው መመህራን ደግሞ ለጥፋቱ ይገባዋል፤ ያስተምረዋል፤ ባህሪውን ያንጻል የሚሉትን ቅጣት መውሰድ የተለመደ እና ማንኛውም ወላጅም ሆነ አሳዳጊ የሚስማማበት ድርጊት ነው።ነገር ግን የብሌን መምህር በወቅቱ ብሌን ላጠፋችው ጥፋት ተመጣጣኝ ያልሆነ በትር በመሰንዘሯ ዛሬ ላይ ብሌን ሁለቱም አይኖቿ እንዳያዩ ሆነ።

“......ትምህርት እወድ ነበር፡፡ ሆኖም የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ማንኛውም ሕጻን የሚያጠፋውን ጥፋት አጠፋለሁ፤ ረብሻለሁ፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን ረብሷል በማለት መምህሬ በማስመሪያ ጭንቅላቴን መምታቷ የዓይን ብርሃኔን አስከወዲያኛው ለማጣቴ ምክንያት ሆነብኝ”በማለት ሁኔታውን ታስረዳለች።

በወቅቱ መምህሬ በሰራሁት ወይም ባጠፋሁት ጥፋት መናደዷን ብቻ ነበር ያየችው የምትለው ብሌን የወሰደችው እርምጃ ምን ሊያስከትል እንደሚቸክል አልገመተችም ነበር።ለእኔ ግን እርምጃው የሕይወቴን አቅጣጫ ያዛባብኝ ሆነ በማለት ስለሁኔታው ታብራራለች።

ብሌን ቅጣቱን ተቀብላ ወደቤት ስትመጣ ራሷን ስታ በመውደቋ ምክንያት እናቷ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ተጋግዘው ወደሕክምና ጣቢያ ይወስዷታል፡፡ እዛም ያገኘችው እርዳታ ከጉዳት የሚያድን አልሆነም። እንደ እሷ አነጋገር ችግሩን አባብሶታል። ያም ሆነ ይህ ግን እናት የልጃቸው የአይን ብርሃን እስከወዲያኛው እንደጠፋ ባወቁ ጊዜ እጅግ ቢደናገጡም፤ ብዙ ቢያዝኑም፤ ብርሃኗ ሊመለስ የሚችልበት እድል ካለ በማለት ያልሄዱበት የሕክምና ተቋም ያላናገሩት ባለሙያ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ብሌን እስከ ሶስተኛ ክፍል ድረስ አብሯት የነበረውን ብርሃኗን ዳግም ላይመለስ ጠፋ።

ከዛ በኋላ ኑሮ ለብሌንም ሆነ ለእናቷ የተመቸ አልሆነም። ትምህርት መማር እንደልቧ ከእኩዮቿ ጋር መቦረቅ አቃታት፤ ይህንን የሚያዩ እናት ደግሞ እጅግ አዘኑ ልባቸው ተሰበረ።ብሌንም ቤት መዋሉን ተያያዘችው።

የብሌን እናት ብቸኛ ልጃቸው በዚህ መልኩ ከእኩዮቿ አንሳ ማየታቸው እረፍት ነሳቸው፡፡ ግን ደግሞ ሊያደርጉ የሚችሉት አንድም ነገር አልነበረም። ብቻ በጭንቀት በብስጭት በቁጭትና በእልህ ራሳቸውን ጎዱ፡፡ ይህ ጉዳታቸው ደግሞ መፍትሔ ከማምጣት ይልቅ ቀን በቀን ወደበሽታ እየወሰዳቸው የመኖር እድሜያቸውን እያሳጠረው መጥቶ ገና በጠዋቱ ለልጃቸውም ምርኩዝ ሳይሆኗት ከዚህ ዓለም በሞት እንዲለዩ ምክንያት ሆናቸው።

ይህ ሁኔታ ለብሌን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው ሆነባት።የአይን ብርሃኗን ማጣቷ ሳያንስ ተንከባካቢና አሳቢ እናቷንም እስከወዲያኛው አጣች። ሃዘኗም በጣም ተባባሰ። ግን ደግሞ እስትንፋስ እስካለች መኖር አይቀርምና ብሌን ነገም ሌላ ቀን ነው በማለት ለመኖር የሚያስችሏትን መንገዶች መፈላለግ ጀመረች። የእናቷ እህት አክስቷም እሷን የማሳደግና የመንከባከብ ኃላፊነትን ተረክበው ወደቤታቸው ወሰዷት።

“.......የእኔ የአይን ብርሃን ማጣት እኔን በብዙ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## በማሳጅና በወጌሻነት ለብዙዎች ፈውስ የሆነች...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ጎድቶኛል፡፡ ተምሬ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ እንዳልደርስ አስቀርቶኛል። ከዛ ሁሉ በላይ ግን እናቴ በእኔ ምክንያት በደረሰባት ሀዘን እርር ብላ እንድትሞትብኝ ሆኗል፤ ይህ በጣም ያሳዝነኛል።ግን ደግሞ የእናቴ ምትክ የሆነችው አክስቴ ምንም እንዳይጎልብኝ አድርጋ ይዛኛለች" ትላለች።

ብሌን የአይን ብርሃኗን ካጣች በኋላ ለአስር ዓመታት ቤት ውስጥ ተቀምጣለች። በእነዚህ ጊዜያት ሰርታ ገቢ ማግኘትን በማሰብ በተማረችው የመጥረጊያና መወልወያ እንዲሁም የቡና ረከቦት ምንጣፍ ስራ ገቢ ማግኘትም ትሞክር ነበር።

".......አያቴ በነበረችበት ወቅት በተለይም የአይን ብርሃኔን ካጣሁ በኋላ ስራ እንዳልፈታ፤ እንዳላዝን በማለት የመጥረጊያ መወልወያ እንዲሁም የቡና ረከቦት ማስቀመጫ ምንጣፍ ስራን አስተምራኝ ነበር። እሱንም እየሰራሁ መጠነኛ ገቢን አገኝ ነበር" ትላለች።

ብሌን በምትሰራው ስራ ገቢ ማግኘቷ እውን ቢሆንም ለስራው የሚያስፈልገው ቦታ ሰፋ ያለ መሆኑና በሌሎችም ምክንያቶች ስራውን ልትገፋበት ሳትችል ቀረች።እናም ከአስር ዓመት በፊት ወዳቋረጠችው የሶስተኛ ክፍል ትምህርት መመለስን አማራጭ አደረገች። በብሬልና በሰዎች ድጋፍ እየታገዘች ትምህርቱን እንደምንም ስምንተኛ ክፍል ማድረስ ቻለች።

".......መጥረጊያና መወልወያ እየሰራሁ እሸጥ ነበር፡፡ አክስቴም መርካቶ በመሄድ ለመስሪያ የሚሆን ግብዓት ታመጣልኝ ነበር፤ ነገር ግን እኔ አክስቴ ጋር ተጠግቼ የምኖር በመሆኑና ትርፍ ቦታም ስላልነበረን፤ ስራውም ሰፋ ያለ ቦታን የሚፈልግ በመሆኑ ተውኩት። እናም ትምህርቴን ለመቀጠል አስቤ ትምህርት ቤት ሄድኩ፤ ያም ቢሆን ግን ብዙ አመርቂ ውጤት ስላላየሁበት ከስምንተኛ ክፍል በላይ ለመማር ሳልችል ቀረሁ " ትላለች።

እናቷ በሕይወት ሳሉ ማዕድን ሚኒስቴር ይሰሩ ነበር፤ በትርፍ ጊዜያቸው ደግሞ ቤት ለቤት እየዞሩ ተማሪዎችን የማስጠናት አገልግሎት ይሰጡም ነበር ። ታዲያ ይህ ስራቸው ካለፉ በኋላ ለልጃቸው እንጀራን የከፈተ ሆነ። ምክንያቱ ደግሞ እሳቸው ያስጠኗት የነበረች ታዳጊ አድጋ ከኢትዮጵያ ውጪ ሄዳ ስትመለስ አስጠኚ መምህሯ ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ፤ ልጃቸውም የአይን ብርሃኗን አጥታ ችግር ላይ እንደሆነች መስማቷ ውለታዋን ለመክፈል አነሳሳት።

"ከአንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም" ይሉት የአባቶቻችን ተረት አይነት ልጅቷም የት አለች ብላ ከልቧ ተነሳስታ አፈላልጋ አገኘቻት። ብሌንን ስታገኛት ከማዘን ወይንም ደግሞ የእለት ጉርሷን ትችልበት ዘንድ ገንዘብ ሰጥታ ከመሸኘት ባለፈ ዘላቂ ነገር ኖሯት በምትችለው አቅም ሰርታ ራሷን የምታስተዳድርበትን መንገድ ማመቻቸት አለብኝ ወደሚል ሃሳብ ነበር የገባችው።ወጣቷ አስባም አልቀረች ብሌንን ፍላጎትና ስሜቷን ብሰራው እለወጥበታለሁ የምትለውን ነገር ጠየቀቻት።ብሌንም ከልጅነቷ ጀምሮ ትወደው እንዲሁም ትሞክር የነበረውን ስራ በመናገር የማሳጅ ትምህርት ብትማር ውጤታማ እንደምትሆን ገለጸችላት።

"........በሚገርም ሁኔታ እንጀራዬ ይሆናል ብዬ ባላስበውም ከድሮ ጀምሮ ግን አያቴ ብርድ ምናምን ትከሻዋን ሲይዛት እሺኝ ትለኛለች ሳሻትም ቶሎ ትድናለች፤ ከዛ ባለፈ ደግሞ በምንኖርበት ግቢ ውስጥ የእግር አቀማመጧ የተበላሸ ሕጻን ልጅ ነበረችና እሷንም ቀን በቀን ዝም አሸቼ ቆማ ሄዳለች፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ማሳጅ ብማር ውጤታማ እሆን ይሆናል የሚል ሀሳብ ጫሩብኝ።

እናቴ በሕይወት በነበረችበት ወቅት ታስጠናት የነበረች ልጅም ወደ እኔ መጥታ ምን እንዳደርግልሽ ወይም በምን ሙያ ሰልጥነሽ መስራት ትፈልጊያለሽ ስትለኝ በቀጥታ ያልኳት ማሳጅ ነበር" በማለት ሁኔታውን ታብራራለች።

ወጣቷም የብሌንን ሕይወት አንድ ርምጃ ወደፊት ሊያራምድ ይችላል ያለችውንና ባለጉዳዩም የመረጠችውን የትምህርት መስክ ትምህርት ቤት በማስገባት ክፍያውን በመክፈልና አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላት በትምህርት የታገዘች የማሳጅና ፊዚዮቴራፒ ባለሙያ ለመሆን በቃች።

ብሌንም ምንም እንኳን የአካል ጉዳቷ እንደምትፈልገው ተንቀሳቅሳ ለመስራት እክል ቢሆንባትም በተማረችው ሙያ ግን ለመታወቅ፤ ሰርታም ለኑሮዋ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ለማሟላት ጥረት ማድረጓን አላቋረጠችም። በዚህ ጥረቷ ደግሞ በተለይም በሰፈሯ አካባቢ በርካታ ሰዎች የተለያዩ ጉዳቶች ሲያጋጥሟቸው ወዳለችበት በመምጣት አልያም ቤታቸው ድረስ መጥታ እርዳታ እንድታደርግላቸው በመጥራት አገልግሎት እያገኙ ከሕመማቸውም እየዳኑ ሲሆን ብሌንም በምትሰራው ስራ በምታገኘው ገቢ ምግቧን ልብሷን እንዲሁም አንዳንድ አስፈላጊ ወጪዎቿን ከሞላ ጎደል እየሸፈነችበት ስለመሆኑ ታስረዳለች።

"......እውነት ለመናገር የማሳጅ ስራ በውስጤ የነበረ ነው፤ በትምህርት ሲታገዝ ደግሞ የበለጠ ሙያውን እንዳወቀው ብሎም የመስራት ፍላጎቱ እንዲያድርብኝ ሆኗል፤ ዛሬ ላይ ሰዎች ሲጠሩኝ ዘይቴን ይዤ ቤት ለቤት በመሄድ አሻለሁ፡፡ አስፈላጊውን ምክርም እለግሳለሁ፤ ለሰጠሁት አገልግሎት በሚከፍሉኝ ክፍያ ደግሞ ወጪዎቼ ለመቻል እሞክራለሁ " በማለት ትናገራለች።

ብሌን የአቅሟን ያህል ትሞክር እንጂ ራቅ ያለ ቦታ ሄዳ እንደልቧ ተንቀሳቅሳ ለመስራት አብሯት የሚሄድ ረዳት ሁሌ አታገኝም፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰዎች በሰፈሯ አካባቢ ስራዋን ቢያውቁትና ቢለምዱትም ሰፋ ባለ ሁኔታ ለመታወቅ አልቻለችም፤ ያም ቢሆን ግን እጇን አጣጥፋ ቁጭ ብላ ተመጽዋች መሆንን አታስብም እንዲሁም እየተንቀሳቀሰች ሰርታ ራሷን መቻል ነው ፍላጎቷ።አሁን ላይ በምታገኘው ገንዘብ ልብስና ጫማዋን ቀለቧን ከመቻል አልፋ የኮንደሚንየም ቤት ባለእድል የሚያደርገውን ቁጠባ እንደ አቅሟ ሳታቋርጥ ትቆጥባለች።

ብሌን በማሳጅ ስራዋ የነርቭ፣ የኩላሊት፣ የልብ የስኳርና የደም ግፊት፣ እንዲሁም አስምና ሳይነስ ሕመሞችን ለማስታገስ የሚጠቅሙ የማሳጅ አይነቶችን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን በመነካካትና በማሸት ታስታግሳለች፤ ይህንንም በትምህርቷ መሰረት በርካታ ሰዎች ላይ ሞክራው ውጤትም እንዳገኘችበት ነው የምትናገረው።

በሌላ በኩል ደግሞ የወገብ በሽታ፤ ወለምታ፤ ውልቃትን በማሸት መፍትሔ ትሰጣለች።ብሌን ከስብራት ውጪ የማትሰራው ስራ እንደሌለም ነው በአንደበቷ የምትናገረው። ብሌን በወር እስከ ሶስት ሰው ድረስ እሰራለሁ ትላለች፡፡

ብሌን ከአክስቷና እንደ እናት ከምታያቸው የእናቷ ጓደኛ በስተቀር ማንም የላትም፤ የኑሮን ውጣ ውረድ ከአካል ጉዳቷ ጋር ደምራ የምትወጣው እሷው እራሷ ናት።በተለይም ራቅ ወዳለ ቦታ ስትጠራ ቦታው ላይ ለመድረስ ትቸገራለች፤ ያም ቢሆን ግን ብሌንን ከመሄድ ሰርቶ ከመብላት አላገዳትም።

".....እንደነገርኩሽ በስራ ቦታዎቼ ሁሉ አብሮኝ የሚንቀሳቀስ ሰው የለኝም፤ ነገር ግን ስራ አግኝቼ እዛ ድረስ እንዴት እሄዳለሁ ብዬ ደግሞ የቀረሁበት ስራም የለም፤ በዚህ አጋጣሚ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሲበዛ ጨዋና ደግ ሕዝብ መሆኑን ለመግለጽ ፈልጋለሁ። ይህንን ያልኩበት ዋናው ምክንያቴ ደግሞ ታክሲ ልሳፈር ስል ቦታውን ይጠቁሙኛል፤ ከመጠቆምም አልፈው ታክሲ ከፍለው ያሳፍሩኛል፤ መንገድ ለማቋረጥ እንኳን ስቆም ተሻምተው ነው የሚያሻግሩኝ፡፡ ይህ ለእኔ ከድጋፍ በላይ የሆነ ትልቅ ነገር ነው።በጣምም ነው የምደሰትበት። በዚህ አጋጣሚ በመንገዴ ሁሉ ለሚያግዙኝ ምስጋናዬ ይድረስልኝ" በማለት ሃሳቧን ትገልጻለች።

> **ብሌን የአቅሟን ያህል ትሞክር እንጂ ራቅ ያለ ቦታ ሄዳ እንደልቧ ተንቀሳቅሳ ለመስራት አብሯት የሚሄድ ረዳት ሁሌ አታገኝም፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰዎች በሰፈሯ አካባቢ ስራዋን ቢያውቁትና ቢለምዷትም ሰፋ ባለ ሁኔታ ለመታወቅ አልቻለችም**

ደስ ያሰኘኝ የስራዬ አጋጣሚ በማለት ብሌን ይህንን ትላለች፤".......ታካሚዬ ሰፈራቸው አየር ጤና አካባቢ ነው፤ ወድቀው እግራቸው ላይ ነው ጉዳት የደረሰው፤ እናም በሕክምና ሲረዱ ቢቆዩም ነገር ግን ውጤት አላመጡም ነበር፤ ችግሩ ተባብሶ በተለይም ባታቸው አካባቢ ስጋቸው ጠፍቶ ቆዳቸው ቀርቶ ነበር፤ እኔም ሁኔታቸውን አይቼ ስብራት አለመሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ የማሻ ድንጋዮቼን በመጠቀም የጉዳቱን ቦታ ማሸት ጀመርኩ፡፡ እየተመላለስኩ አገልግሎት ከሰጠሁ በኋላም አሁን ላይ ሕመምተኛው ቆመው መራመድ ጀምረዋል "በማለት ስራዋ ውጤታማ ሲሆን የሚሰማትን ላቅ ያለ ደስታ ትናገራለች።

ሙያዬ የተከበረና ትልቅ ለብዙ ሰዎች የችግራቸው መፍትሔ ቢሆንም እኔ ግን መስሪያ ቦታ ማጣቴና ሰዎችን በሰፊው ማገልገል አለመቻሌ በጣም ያሳዝነኛል የምትለው ብሌን ዛሬ ላይ እኔን አይቶ ማድነቅ፤ አልያም ከንፈር መጦ መሄድ ጥቅም አልባ ነው ትንሽም ብትሆን ሰርቼ ለመለወጥ የሚያስችለኝ ቦታ በመንግስትም ይሁን በግለሰቦች ቢመቻችልኝ ለብዙዎች መፍትሔ መሆን እችላለሁ በማለት መልዕክቷን ታስተላልፋለች።

ብሌን በማሳጅ ሙያ በሰርተፍኬት ደረጃ ተመርቃለች፡፡ ለምን ተቀጥረሽ አትሰሪም የሚል ጥያቄ ከብዙዎች እንደሚመጣላት ትናግራ ነገር ግን እሷ ይህ እንደማይሆን ነው የምትናገረው ምክንያቷ ደግሞ "......... ማሳጅ ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡ የዛኑ ያህል ደግሞ ለእኩይ ተግባር የሚጠቀሙበት ብዙዎች ናቸው፤ እኔ ደግሞ አካል ጉዳተኛ ነኝ፡፡ ጉዳቴ ደግሞ ማየት መሳኔ ነው፤ ስለዚህ ምንም ዓይነት ጾታዊ ጥቃት ቢደርስብኝ መቋቋም ስለማልችል መቀጠር አልፈልግም።አንዳንድ ቦታ ስጠራ እንደውም አክስቴን ሁሉ አስከትዬ የምሄድበት አጋጣሚ አለ "በማለት ተቀጥራ ላለመስራቷ ምክንያቷን ትናገራለች።

ብሌን አካል ጉዳተኛ በመሆኑ የተለያዩ የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማኅበርን ለማነጋገር በእነሱም በኩል አንዳንድ ድጋፎችን ለማግኘት ያደረገችው ጥረት አለመሳካቱን ትናገራለች።በተለይም ወደ አይነስውራን ብሔራዊ ማኅበር ሄዳ ያቀረበችው ጥያቄ እንደውም አስከፊ ምላሽ ይዞባት ስለመምጣቱም ነው የምትገልጸው።

".......እውነት ለመናገር በተለያዩ አካል ጉዳቶች ስያሜ የሚቋቋሙ ብሔራዊ ማኅበራት ብዙ ናቸው፤ በእርግጥ የሚጠቀምባቸው የተሻለ ነገርን የሚያገኙባቸው አካል ጉዳተኛ ሊኖር ይችላል።እኔ ግን የአባልነት ምዝገባን ባደርገም ከእነሱ ያገኘሁት አንድም ድጋፍ የለም።እንደውም የአይነ ስውራን ብሔራዊ ማኅበርን ሳናግራቸው አባል አድርገው ከመዘገቡኝ በኋላ አንቺ ማየት ትችያለሽ የሚል ነውረኛ ምላሽ ነው የሰጡኝ።እኔም ብትፈልጉ በሕክምና አረጋግጡ ብዬ ተውኳቸው።በእጄ የምይዘውን ብትር እንኳን የገዛችለኝ የእናቴ ጓደኛ ናት።እኔ ስም ካልሆነ በቀር ያገኘሁት አንዳችም ድጋፍ የለም አሁን ላይ ስለሰለቸኝ ወደ እነሱም አልሄድም "በማለት ሁኔታውን ታስረዳለች።

### መልዕክት

አካል ጉዳተኛ ሁሉ የተሰጠውን ተቀብሎ ራሱን የሚችልበትን መንገድ ነው መፈለግ ያለበት፡፡ በልመና አልያም በእርዳታ የሚያልፍ ችግር የለም።ከዛ ይልቅ በሚቻለው መጠን ጥሮ ተጣጥሮ መኖርን ምርጫ ማድረግ ያስከብራል።

አካል ጉዳተኝነት በየትኛውም አጋጣሚ በማንም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችል መሆኑን አምኖ ለምን እኔ ላይ ከሚል ሃሳብ በመላቀቅና ራስን ነጻ አድርጎ በመኖር ሕይወትን መግፋት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩልም በአካል ጉዳተኞች ስም የተቋቋሙ ድርጅቶችና ሌሎችም ለቆሙለት ዓላማ ታማኝ በመሆን በእውነትና በሀቅ የተቸገሩት የሚረዱበት ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን ችለው ለሌሎች የሚተርፉበትን ሁኔታዎች ቢያመቻቹ በማለት መልዕክቷን አስተላልፋለች።

# ቱሪዝም-

## የአድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ሌላኛው መልክ

**ዳግም ከበደ**




በጣሊያን ወረራ ምክንያት የተደረገው የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያውያን አርበኞች ድል አድራጊነት ከተካሄደ 128 ዓመታትን አስቆጠረ። ከአንድ ክፍለ ዘመን የተሻገረው ይህ ድልም በትውልድ ቅብብሎሽ ታሪኩ ሲዘከርና የጀግንነት ተምሳሌት ተደርጎ ሲቆጠር ይኖራል። ከኢትዮጵያውያን ጀግንነት ተሻግሮ የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት የፓን አፍሪካ መሰረት ለመሆንም በቅቷል።

የአድዋ ድል ለበርካታ አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ነግሶ ተገቢውን ክብር አግኝቶ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ሲከበርና ሲዘከር ነበር። ይህ ድል የግዙፍነቱን ያህል በመንግስታት የሚገባውን ስፍራ አግኝቶ የሚመጥነው መታሰቢያ ባይገነባለትም ኢትዮጵያውያን ግን አንድም ቀን የአባቶቻቸውን የጀግንነት ታሪክ ዘንግተውት አያውቁም ነበር። ታሪኩን ለመዘከር ወደ አደባባይ በመውጣት ክፍለ ዘመን ለተሻገሩ ዓመታት ሲያስታውሱት ነበር።

የአድዋ ድል አሁን ከዜጎች ልብ ተሻግሮ በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል። ለድሉ የሚመጥን መታሰቢያም ኢትዮጵያውያን ወደ ጦርነቱ ለመሄድ በአንድነት በተሰባሰቡበት መሀል አዲስ አበባ ፒያሳ ተገንብቶለታል። ይህ መታሰቢያ የጀግኖች አርበኞች ድልን ዛሬ በሚመስል መልኩ ከማስታወስ ባሻገር ትውልዱ እንዲበረታ፣ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል መሆኑን እንዲገነዘብ፣ ሕብረትና አንድነት ለድል እንደሚያበቃ፣ ኢትዮጵያ የመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ምሳሌ እንደሆነች፣ የአባቶቹን ብልህነት፣ አሸናፊነትና በፈተናዎች መፅናት እንዲያውቅ ህያው ሆኖ የሚቆም ነው።

የአድዋ ድል መታሰቢያ ብዙ መልክ አለው። አንድም የጀግኖች አርበኞችን መዘከሪያ፣ ሁለትም ለአዲሱ ትውልድ ማስተማሪያነት ግዙፍ ፋይዳ ያለው ነው። ከሳምንት በፊት በምረቃ ስነስርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ‹‹ከታሪክ ታሪክን መዘከር ብቻ ሳይሆን ከታሪክ መማር አለብን›› በማለት መልዕክት አስተላልፈው ነበር።

መልዕክቱ የሚያሳየን በአድዋ ጦርነት ላይ ከተመዘገበ ድልም ያለፈ ትርጉም እንዳለው ነው። ይህን ለመረዳት የቀደመውን የአባቶችን ጥበብ፣ ጀግንነት፣ ትዕግስት፣ ዲፕሎማሲ እና ለጠላት ትምህርት የመሆን ተግባርን በቅርቡ ከተገነባው የአድዋ ድል መታሰቢያ ማግኘት ይቻላል። ይህ መታሰቢያ በመላው ዓለም ሕዝቦች የሚጎበኝ ግዙፍ የታሪክ ትምህርት ቤት (ሙዚየም) ነው። በመሆኑም በቱሪዝም ዘርፍ አንድ የታሪክ ክፍል ሆኖ እንደሚያገለግል ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ለዚህም ሙዚየሙን ለአገር ውስጥና ለመላው ዓለም ሕዝብ ማስተዋወቅ የሚኖረውን ፋይዳ የዝግጅት ክፍላችን ከዚህ እንደሚከተለው ለመዳሰስ ይወድዳል።

ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ናቸው። የአድዋን ድልን የሚዘክረው (አድዋ ዜሮ ዜሮ) ሙዚየም በፒያሳ እምብርት ላይ ሲታነፅ መስሪያቤታቸው በአማካሪነት እንደ አንድ ባለድርሻ ተሳታፊ ነበር። እርሳቸው የሙዚየም ግንባታውን በማስመልከት ሲናገሩ፤ በተገነባው መታሰቢያ በአድዋ ዘመቻ ወቅት ጀግኖች አርበኞች ሴቶችም ወንዶቹም፣ ገበሬዎችም ይዘውት የዘመቱት ጦር መሳሪያና ሌሎችም ቅርሶችን በሙዚየሙ ውስጥ አሰባስቦ ይዟል።

‹‹ሙዚየሙ ከጦር መሳሪያ እስከ እለት ምግብ መመገቢያ ያሉት የአድዋ ዘማች አርበኞች መገልገያ በመያዙ ያንን ለትውልድ ማሳየት ይገባል›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው፤ ይህ መሆኑ ታሪክን ለማሳየት እንደሚረዳ ይናገራሉ። የተማረኩ መድፎች፣ የጦር መሳሪዎች የተጠቀሙባቸው ጎራዴዎች መኖራቸውን በመግለፅ ይህ በግዜው የነበረውን ሁነት ለማሳየት እንደሚረዳ ይገልፃሉ።

አድዋ ከቅርሶቹ ባሻገር ለትውልድና ለቀሪው ዓለም ማሳየት ይቻላል የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ ለዚህ ስነ ጥበብ አንዱ መንገድ መሆኑን ይናገራሉ። በአድዋ መታሰቢያ ውስጥ የተገነቡ ቅርፆች (የጀግኖች መሪዎችና የጦር ጀነራሎች ሀውልቶች) መኖራቸውን ይናገራሉ። ቅርፆቹ የተሰሩት በምናባዊነት ሳይሆን በወቅቱ ከነበሩ ስዕሎች ያካተተ መሆኑን ይገልፃሉ።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የአድዋ ድል መታሰቢያ በውስጡ በርካታ ቅርሶችን፣ መስህቦችን እና ታሪካዊ እውነታዎችን ይዟል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የወቅቱን የአድዋ ጦርነት በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚያሳይ (ቨርቹዋል ሪያሊቲ)፣ የአፄ ሚኒሊክና የእቴጌ ጣይቱ ሀውልት፣ የ12 ጦር አዝማች ጀነራሎች ሀውልት፣ የፓን አፍሪካኒዝም ገላጭ ምስሎች፣ በመታሰቢያ ሙዚየሙ በርካታ አዳራሾች ሲኖሩ ባለሙያዎች እነዚህ አዳራሾች የማይስ (ስብሰባ ቱሪዝም) እንደሚያሳድግ ሲገልፁ ተደምጠዋል።

አቶ እንደኛነው አሰፋ የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ነው። እርሱ እንደሚለው፤ መታሰቢያው በዋነኝነት የአድዋን ድል እና ታሪኩን ጠብቆ ለማቆየት፣ ለትውልድ ለማስተማር፣ ለዓለም ዓቀፍ ጎብኚዎች እድል ለመፍጠር ታስቦ መሰራቱን ይናገራል። ማኅበሩና በውስጡ በዓባልነት የሚሳተፉት አስጎብኚዎች ይህንን መስህብ ከኢትዮጵያ የድል ታሪክነቱ ባሻገር ለቱሪዝም ትልቅ ፋይዳ እንዳለው እንደሚያምኑም ይገልፃል።

‹‹ቱሪዝም ባሕል፣ ተፈጥሮ፣ ታሪክን አጉልቶ የሚያሳይ ነው›› የሚለው የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፤ አድዋም ከታሪክ ዘርፍ የሚመደብ ለዓለም ሕዝብ በኩራት ልናሳየው የምንችለው የድል ታሪክ መሆኑን ይገልፃል። አንዳንድ አገራት መጥፎ ታሪክ የደረሰባቸው ቢሆንም እርሱን ለዓለም ሕዝብ በሙዚየምነት በማሳየት ታሪኩን ከማስተዋወቅ ባሻገር የቱሪዝም አንዱ ዘርፍ አድርገው እንደሚወስዱት ይናገራል። በሩዋንዳ የደረሰው የዘር ጭፍጨፋን እንደ ምሳሌ ያነሳል። በማሊ፣ ሴኔጋልና ሌሎች የምዕራብ አፍሪካ አገራት ውስጥ በቅኝ ግዛት ዘመን የነበረውን ታሪክ፣ የደረሰባቸውን በደል፣ ሲያደርጉት የነበረውን ተጋድሎ (የባሪያ ንግድና የቅኝ ግዛት ታሪካዊ ማስታወሻ) እንዲሁም አጠቃላይ ታሪክ በሙዚየሞች እና በልዩ ልዩ ታሪካዊ መገለጫዎች ለጎብኚዎች ይፋ እንዳደረጉም ያስረዳል። ትውልዱን ከቀደመው ታሪክ ከማስተማራቸውም ባሻገር እንደ አንድ የቱሪዝም የገቢ ምንጭ እና የገፅታ ግንባታ እንደሚጠቀሙበት ያስረዳል።

‹‹እኛ ደግሞ የአኩሪ ድል ባለቤት ነን›› የሚለው አቶ እንደእኛነው አሰፋ፤ ይህንን የአድዋ ድል ጀግንነት፣ የአርበኞችን ተጋድሎና የነፃነት ቀንዲል እንደ አንድ የቱሪዝም አካል አድርጎ ታሪኩን ለዓለም ሕዝብ ማሳየት እና ለአገር ገፅታ ግንባታ፣ ለትውልድ መማሪያና ለፓን አፍሪካኒዝም ፍልስፍና መሰረት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይናገራል።

የአድዋ ድል ብዙ መልክ አለው። ከዚህ ወስጥ አንዱ አድዋን ልክ እንደ አንድ የቱሪዝም መስህብ መጠቀም ነው። አቶ እንደእኛነውም ይህን ሀሳብ ይጋራል። አስጎብኚዎች፣ የታሪክ ፀሀፊዎች፣ የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎች የአድዋን ድል ለአገር ገፅታ መገንቢያ፣ ለቱሪስት ፍሰት ማደግና ለኢኮኖሚ ምንጭ ለማዋል በትብብር መስራት እንደሚጠበቅባቸው ያስረዳል። አድዋንና ሌሎችም የኢትዮጵያ ታሪኮች በመሰል ማራኪ መታሰቢያዎች በአግባቡ ሰንዶና አዘጋጅቶ ለቱሪዝም መስህብነት ማዋል እንደሚገባም ይገልፃል።

የአድዋ መታሰቢያ ለማኅበረሰቡ የተለያዩ ጥቅሞችን የሚሰጡ እድሎችን ይዞ መምጣቱን የሚናገረው የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፤ ኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኮንፍረንስ ማዕከል እንደመሆኗ የአድዋ መታሰቢያ ግንባታም ያንን ታሳቢ በማድረግ ለግንኙነት ምቹ የሆኑና የማይስ ቱሪዝም አቅምን የሚያሳድጉ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉ አዳራሾችን ጭምር በመያዙ ፋይዳው ጉልህ መሆኑን ያስረዳል። የአድዋን ድል ታሪክ እያዩ፣ ታሪክን እየዘከሩ እግረ ስመንገድ ስብሰባዎችን መካፈልና ልዩ ልዩ ተግባራት ላይ መታደም ስለሚቻል ፕሮጀክቱን ልዩ እንደሚያደርገው ይገልፃል።

‹‹የአድዋ ሙዚየም መገንባቱ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የጥቁር ሕዝብ ድል መሆኑን ማሳየት ይገባናል›› የሚለው አቶ እንደኛነው አሰፋ፤ ፕሮጀክቱንም ሆነ የአድዋን ታሪክ በዚህ አግባብ ለዓለም ሕዝብ ማስተዋወቅ እንደሚገባ ይመክራል። የቱሪስት አስጎብኚዎችም የአድዋ ሙዚየም በአዲስ አበባ ውስጥ አዲስ የመስህብ አማራጭ መሆኑን ገልፀው እርሱን እንደ አንድ የቱሪዝም ምርትና መስህብ አማራጭ ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ ልንጠቀምበት እንደሚገባ ያሳስባል።

አድዋ በመላው ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ የነፃነት ጮራ የፈነጠቀ ድል ተደርጎ ይቆጠራል የሚለው የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ኢትዮጵያውያን ደግሞ በባለቤትነት ለትውልድ ማሻገር ይገባል ይላል። በተለይ በቱሪዝሙ ዘርፍ ላይ አስጎብኚ ባለሙያዎች አሁን የተገነባውን የአድዋ ዜሮ ዜሮ ፕሮጀክት (ሙዚየም) መነሻ በማድረግ ጎብኚዎች ኢትዮጵያን ብሎም የድሉን ታሪክ እንዲጎበኙ በተገቢው መንገድ ማስተዋወቅ እንዳለባቸው ይገልፃል። በጥቁር ሕዝብ ትግል ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ የሚይዘው የአድዋ ድል መሆኑን በማንሳትም ድሉን ሁሉም ሰው የራሱ እንዲያደርገውና ኢትዮጵያንም በዚያ መልኩ እንዲመለከት መስራት እንደሚጠበቅብን ምክረ ሀሳቡን ይሰጣል።

የቱሪስት አስጎብኚዎች ማኅበር በአዲስ አበባ እምብርት ላይ የተገነባው መታሰቢያ የአድዋ ድልን በሚገባ የሚገልፅና ተገቢ ፕሮጀክት መሆኑን ያምናል የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርም ይናገራሉ። ከዚህ ባሻገር ይህንን ታሪክ በዚህ ሙዚየም ብቻ መወሰን እንደማይገባ ገልፀው ሌሎች ድሉንና ታሪኩን አጉልተው የሚያሳዩ ተጨማሪ ፕሮጀክቶች በተለያዩ ቦታዎች መሰራት እንዳለባቸው ነው ያስረዳው።

‹‹የአድዋ ድልና ታሪካዊ እውነቶችን የቱሪስት አስጎብኚዎች በሚገባ መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል›› የሚሉት ፕሬዚዳንቱ ይህ ሲሆን ለጎብኚዎች ታሪካዊ ሁነቶቹን ማሳወቅና ትውልድን ማስተማር እንደሚችሉ ይገልፃሉ። በመሆኑም አዲስ የተገነባውን ሙዚየም ሁሉም ባለሙያዎች ሊያዩትና እራሳቸውን ሊያዘጋጁበት እንደሚገባ አሳስበዋል።

**እንደ መውጫ**

የአድዋ ድል 128ተኛ ዓመቱን ያስቆጠረ ቢሆንም ሙዚየሙ ተገንብቶ እስከተጠናቀቀበት ግዜ ድረስ ምንን አይነት ግዙፍ መታሰቢያ ሳይገነባለት ቆይቷል። አሁን ግን የአድዋ ሙዚየም (አድዋ ዜሮ ዜሮ) በመንግስት ፕሮጀክት ተገንብቶ ለእይታ ክፍት ተደርጓል። የካቲት 23 ቀን በብሄራዊ በዓልነት በድምቀት የድል በዓሉ ሲከበርም በሙዚየሙ ደማቅ ስነስርዓት ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል።

የምረቃ ስነስርዓቱ እለት ሙዚየም ግንባታውን አስመልክቶ ንግግርን ያደረጉት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ፤ በዓድዋ ጦርነት ኢትዮጵያውያን ልዩነትን ወደ ጎን በመተው በአንድነት ወደ ዓውደ ውጊያው ተምመዋል፤ በዚህም የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የነፃነት ቀንዲል የሆነውን የዓድዋ ድልን አስመዝግበዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ የጀግንነት ገድል የደመቀበት በማለትም፤ ተበታትነው የነበሩ የታሪክ ማስረጃዎች የተሰበሰቡበት፤ የተረሱ የታወሱበት መሆኑን ገልፀው ነበር። የዓድዋ ድል መታሰቢያ ጀግኖችን በሚገባቸው ከፍታ ያስቀመጠ መሆኑን ጠቅሰውም ትውልዱ በአንድነት ሆኖ ማሸነፍንና የሀገር ፍቅርን የሚማርበት መሆኑንም አንስተው ነበር። የዓድዋ ድል መታሰቢያ መላ ኢትዮጵያውያን በአንድ ቋንቋ እንዲግባቡ የማድረግ ኃይል ያለው መሆኑን በመግለጽ ትናንትን ከዛሬ ዛሬን ከነገ የሚያስተሳስር ድልድይ በመሆኑ ለመጪው ትውልድ ስጦታ መሆኑን ገልፀዋል።

የመታሰቢያ ሙዚየሙም ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ከመላው ዓለም ታሪኩን ለማወቅ ለሚመጡ ጎብኚዎች ከየካቲት 5 ጀምሮ ክፍት እንደሆነ ተነግሯል። ከወዲሁ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮች፣ በአፍሪካ ሕብረት ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ የመጡ ሚኒስትሮች እና ልዩ ልዩ ዲፕሎማትን ጨምሮ ለቁጥር በበዙ ቱሪስቶች እየተጎበኘ ይገኛል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የካቲት ወር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ

**ዋስልኝ አየለ**

የየካቲት ወር ‹‹የጥቁር ሕዝቦች ወር›› እየተባለም ይጠራል። የጥቁር ሕዝቦች የመብት ማስከበር ታሪኮች የሚነገሩበት ነው። በተለይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ደግሞ በብዙ ታሪካዊ ክስተቶች የታጨቀ ወር ነው። ከአገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፍ ያሉ የኢትዮጵያ ታሪኮች የተመዘገቡበት ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ይህን ወር ገናና የሚያደርገው የዓድዋ ታሪክ ነው። ስለዓድዋ ጊዜው ሲደርስ የምናወራ ይሆናል። ከዚያ በፊት የየካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያም የየካቲት ወር ሌላው መለያ ነው። የካቲት 26 የካራማራ የድል ታሪክም አለ። ጊዜው ሲደርስ በዝርዝር እናያቸዋለን።

ወደ አገር ውስጥ ጉዳዮች ብቻ ስንመጣ ደግሞ የካቲት 11 የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ምሥረታ ታሪክ አለ። በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ንጉሣዊ ሥርዓቱን ለመጣል የተቀጣጠለው የደርግ አብዮት የተጀመረውም በዚሁ በወርሃ የካቲት ነው፡፡

ከእነዚህ የየካቲት ታሪካዊ ክስተቶች የወሩን ስም የያዘው ‹‹የየካቲት አብዮት›› የሚባለው ነው። ይህ አብዮት በወርሃ የካቲት ስለተቀጣጠለ በ1፣ በ2፣ በ3፣ ወይም በ20 ምናምን ተብሎ ሳይሆን የሚገለጸው በጥቅሉ የየካቲት አብዮት ተብሎ ነው።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ50 ዓመታት በፊት በወርሃ የካቲት 1966 ዓ.ም የነበረውን የየካቲት አብዮት እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን እናስታውስ፡፡

ከ106 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም የነበረው ክስተት የእቴጌ ጣይቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ነው።

‹‹ብርሃን ዘ ኢትዮጵያ›› በሚል ቅፅል ስም የሚታወቁት እቴጌ ጣይቱ ከአባታቸው ደጃዝማች ብጡል ኃይለ ማርያም እና ከእናታቸው ወይዘሮ የውብዳር ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም በጌምድር ውስጥ ደብረታቦር ከተማ ተወለዱ።

ወደ ፖለቲካዊ ታሪካቸው እንሂድና፤ የፋሲካ ዕለት ሚያዝያ 25 ቀን 1875 ዓ.ም በአንኮበር መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ከአጼ ምኒልክ ጋር ቅዱስ ቁርባን ተቀብለው ተጋቡ። ንጉሡ ‹‹አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ›› የሚለውን ስም በተቀዳጁ በማግሥቱ ጥቅምት 27 ቀን 1882 ዓ.ም ወይዘሮ ጣይቱ ብጡል እቴጌ ተብለው ተሰየሙ።

ከእቴጌ ጣይቱ የፖለቲካ ተሳትፎዎች ጎልቶ የሚታየው፤ ኢትዮጵያ ሚያዝያ 25 ቀን 1981 ዓ.ም በውጫሌ ላይ ከኢጣሊያ ጋር በተፈራረመችው ውል ውስጥ በኢጣሊያንኛው ትርጉም ሀገሪቷን ነፃነት እንደሌላት ጥገኛ በማስመሰል ዓላማ ላይ የተመረኮዘ ውንብድና መኖሩ ሲታወቅ በተናገሩት ነው።

የጣሊያንን ሴራ ከተረዱ በኋላ «እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም። ሆኖም ይህን ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ጥገኛ የሚያደርግ ውል ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ» የሚል አቋማቸው በታሪክ ሰነድ በደማቁ ተጽፏል።

እቴጌ ጣይቱ ለኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መረጋጋት የሚያረጋግጥ የሀገር ግንባታ ተግባሮች በማከናወን ረገድና የአዲስ አበባ ከተማ መቆርቆር በእቴጌ ጣይቱ ከተጠናቀቁት የግንባታ ተግባሮች አንዱ ነው። ከሚታወሱባቸው አንዱ ደግሞ ፒያሳ ያለው ጣይቱ ሆቴል ነው።

በልጅ እያሱ አስተዳደር ዘመን እቴጌ ጣይቱ ከቤተ መንግሥት ተወግደው በግዞት ላይ ለአንድ ዓመት በላይ እንደተቀመጡ ይነገራል። ሆኖም ታማኝ አሽከሮቻቸውና መላው ሠራዊት የእቴጌነታቸውን ልዕልና አላጐደለባቸውም። መሳፍንቱ መኳንንቱና ወይዛዝርቱም ቢሆኑ ተገቢውን አክብሮት ሳይነፍጓቸው ዕለት በዕለት ይጠይቋቸው ነበር።

የልጅ እያሱ ሥልጣን ብዙም ሳይቆይ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም የሚኒስትሮች ካቢኔ ዘውዲቱ ምኒልክ ንግሥተ ነገሥታት ተብለው መንግሥቱን በመምራት እንዲተኳቸው መደረጉ ለእቴጌ ጣይቱ ታላቅ ድል ሆነ። በመሆኑም የእቴጌም የእስራት ቀንበር ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ሊወድቅላቸው ቻለ። ንግሥት ዘውዲቱ ሥልጣናቸው ተዳክሞ ትዕዛዛቸው እንዳይዛባ በማለት ከተጓዙበት ከእንጦጦ ሳይቀር ምክር መለገሳቸውን አላቋረጡም ነበር።

እቴጌ ጣይቱ የደረሰባቸውን ፈተና ሁሉ በትዕግስት ተቀብለው ጥቂት እፎይ ካሉ በኋላ ከአፄ ምኒልክ ጐን ሆነው የኢትዮጵያን አንድነትና ጥንካሬ ለማረጋገጥ ሲታገሉ ያለፉት ዘመን ከዕለታት አንድ ቀን ትዝ ስላላቸው ከሰገነት ላይ ብቅ ብለው «ያ ቤት የትኛው ነው?» ብለው ሲጠይቁ ከደንገጡሮቹ አንዷ «የእመቤቴ እልፍኝ ግምጃ ቤት ነበር» አለች። እሳቸውም ትንሽ ተከዝ ብለው ከቆዩ በኋላ ቀበል በማድረግ «ነበር ለካስ እንዲህ ቅርብ ኖሯል» አሉ ይባላል። ይህም እንደ አባባል ሆኖ ይነገርላቸዋል፡፡

ከ87 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 7 ቀን 1929 ዓ.ም ሆሎታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ተመሰረተ። የሆለታ ገነት ጦር አካዳሚ በ1928 ዓ.ም በቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ስም በአምስት የስዊድን መኮንን አሰልጣኞች እገዛ ስራውን ጀመረ። ሆኖም ግን ፋሽስት ጣልያን ኢትዮጵያን በመውረሩ የጦር ማሰልጠኛው በአግባቡ ስራውን ማከናወን አልቻለም። በወቅቱ ሥልጠና ይከታተሉ የነበሩ ሠልጣኞች የመጀመሪያ ዘመናዊ ጦር ሰልጣኝ ስለነበሩ ብርቅ ተዋጊዎች ነበሩ። ከማሰልጠኛው ውስጥ የነበሩ ሰልጣኞችም ሆኑ ስልጠናውን ያጠናቀቁ ‹‹የጥቁር አንበሳ ጦር›› በሚል አዲስ የአርበኞች እንቅስቃሴ በተለይ በምዕራብ ኢትዮጵያ ጀመሩ።

የጥቁር አንበሳ ጦር በፋሽስት ጣልያን ወረራ ወቅት በአርበኝነት የተሳተፉ የሆለታ ገነት ጦር ምሩቃን እና በውጭ የተማሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን የመሰረቱት ፀረ ፋሽስት እንቅስቃሴ ነው። በጣልያን ላይ ዘመናዊ የጦር ውጊያ በማሳየት ብቻ ሳይሆን በጥንታዊ መንገድ ለሚዋጋው የኢትዮጵያ ገበሬ አርበኛ ዘመናዊ የውጊያ ስልትን በማስተማር የጥቁር አንበሳ ጦር ያደረገው አስተዋፅኦ ቀላል አልነበረም።

የሆሎታ ገነት ጦር አካዳሚ ተመልሶ የተመሰረተው ጣልያን ከተባረረ በኋላ ንጉሰ ነገሥቱ ተመልሰው ከመጡ በኋላ በ1935 ዓ.ም ነበር። የጥቁር አንበሳ የጦር አካዳሚ ‹‹ሆለታ ገነት ጦር አካዳሚ›› የሚል ስያሜ ያገኘውም ደርግ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ነበር።

የሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት በአፍሪካ አንጋፋው በዓለማችንም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊት ከተመሰረቱ ጥቂት የጦር ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ የጦር ትምህርት ቤት በዘመነ ኢህአዴግ (1990 ዓ.ም) ለግማሽ ክፍለ ዘመን የቆየው ‹‹ሆለታ ገነት ጦር›› ስያሜ ወደ ሐየሎም አርአያ የጦር ማሰልጠኛ ተቀይሮ እንደነበር ይታወሳል።

**በዚሁ ወደ ‹‹የየካቲት አብዮት›› ታሪክ እንሂድ።**

ከዛሬ 50 ዓመት በፊት በወርሃ የካቲት 1966 ዓ.ም አዲስ አበባ በታክሲ አሽከርካሪዎች፣ በመምህራን፣ በሠራተኞች፣ በወጣቶች፣ በተማሪዎች፣ በወታደሮች በጥቅሉ በሕዝባዊ አብዮት ተናወጠች። መሬት ለአራሹ፣ የዴሞክራሲ መብት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የብሔሮች እኩልነት፣ የሴቶች እኩልነት ከፍ ተደርገው ተጮኹላቸው፣ ተዘመረላቸው።

የካቲት 1966 ዓ.ም የፈነዳው እሳተ ገሞራ አድማሱን አስፍቶ ኢትዮጵያ ለሺህ ዘመናት የተዳደረችበትን የዘውድና የአፄ ሥርዓት የገረሰሰበት አብዮት ተወለደ።

የካቲት አዝሎት የነበረው ሕዝባዊ ተስፋ መጠነ ሰፊ ነበር። በረሃብ ዘወትር የሚጠቃው ሕዝብ በቀን ሦስት ጊዜ የሚመገበው የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ፣ ጤናው እንዲሟላ፣ ትምህርት ያልደረሰው ወገን ትምህርት እንዲያገኝ፣ የነበረው የትምህርት ሥርዓትም የተሟላና ከምርትና ከዕድገት ጋር የተያያዘ እንዲሆን፣ ንጹህ ውሃ፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆን ተስፋና ምኞትን ተሸክሞ ነበር።

እነዚህ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተስፋዎች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ደግሞ የካቲት ፖለቲካዊ ተስፋም አንግቦ ነበር። ማን እቅዱን ያወጣል? ማን እቅዱን ይተቻል? ማን እቅዱን ያስፈጽማል? ማንስ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ሁሉ የካቲት ተስፋዊ መልስ ሰጥቶ ነበር።

ሥልጣን የሕዝብ እንዲሆን፣ አገሪቱ በሕዝብ በተመረጡ ዜጎች እንድትተዳደርና ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት፣ ዳኝነት ፍትሃዊ በሆነና ነፃ በሆነ መልኩ እንዲሰፋፋ፣ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች፤ ማለትም በፖለቲካ ድርጅትም ሆነ በሠራተኛ ማኅበር የመደራጀት መብት እንዲከበር፣ በነፃነት የመጻፍ፣ የመወያየት ... ወዘተ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ የካቲት ተስፋውን ሰንቆ ነበር።

የካቲት 1966 ዓ.ም ኢትዮጵያውን ለመለወጥ የትግል ችቦ የተለኮሰበት፤ አርሶ አደሮች ከባላባታዊ የጭሰኝነት ሕይወት ለመላቀቅ ያመጹበት፣ ለተመጣጣኝ ሥራ ተመጣጣኝ ክፍያ የተጠየቀበት፣ መምህራን አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ «ሴክተር ሪቪው»ን የተቃወሙበትና በማኅበራቸው ደህንነት የሞገቱበት፣ ታክሲ ነጂዎች በነዳጅ ጭማሪ ምክንያት ሥራ ያቆሙበት፣ ሙስሊሞች የሃይማኖት እኩልነት ብለው በአደባባይ ሰልፍ የወጡበት፣ ተማሪዎችና ተራማጅ ኃይሎች ‹‹መሬት ለአራሹ›› መፈክርን ከፍ አድርገው ሥር ነቀል ለውጥ የጠየቁበት ነበር።

**የየካቲቱ 1966 ዓ.ም ሕዝባዊ አብዮት ወደ ወታደራዊ አብዮት ተሸጋገረ። በሦስት ወር ጉዞውም የንጉሱን 60 ሹማምንት ያለፍርድ ገድሎ በርካታ እርምጃዎችን ወሰደ። ንጉሱን ከስልጣን በማውረድ እራሱን ደርግ ብሎ በመሰየም ብቸኛው የኢትዮጵያ መንግስት ሆነ**

የየካቲቱ 1966 ዓ.ም ሕዝባዊ አብዮት ወደ ወታደራዊ አብዮት ተሸጋገረ። በሦስት ወር ጉዞውም የንጉሱን 60 ሹማምንት ያለፍርድ ገድሎ በርካታ እርምጃዎችን ወሰደ። ንጉሱን ከስልጣን በማውረድ እራሱን ደርግ ብሎ በመሰየም ብቸኛው የኢትዮጵያ መንግስት ሆነ።

አማካሪዎቹም በዚሁ ሹም ሽር ከስልጣን ተካፋይነት ወደ ሁለተኛ ደረጃ አማካሪነት ወረዱ። በዚህ ሁኔታ የመጣው ደርግ 17 ዓመት ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር መጀመሪያ ‹‹ኢትዮጵያ ትቅደም›› በኋላ ‹‹ሶሻሊስት ሪፑብሊክ›› እየፈጠረ ቢሄድም እየቆየ ግን እሱም በተራው ተቃዋሚዎች ተፈጠሩበት።

በዋና ተቃዋሚነት ኢሕአፓ በደርጉ ስርም እነ መኢሶን፣ ወዝ ሊግና ሌሎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጨምሮ በኢትዮጵያ የአብዮት ተውኔት መድረክ ላይ ያዋጣል ያሉትን የትግል ስልትና ዘዴ ቢከተሉም የደርግ መንግስት ወታደራዊ ባህሪው አይሎበት ሲጨፋጨፉ ቆይተዋል።

የደርግ መንግስት በተራው በስልጣን ዘመኑ የተነሱትን አበይት ጥያቄዎች ለመመለስ ከሰላም ውይይት ይልቅ ጦር ሰባቂ ጎራዴ ታጣቂ በመሆኑ ዘመኑን ሙሉ አገሪቱን ያላባራ ጦርነት ውስጥ ከተታት።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደሚሉት፤ ከ1966 እስከ 1968 ዓ.ም ድረስ ባሉት ሁለት ዓመታት ደርግ ከያዘው ርዕዮት ጋር ለመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ከማንም ያላነሰ ክህሎት አለኝ ለማለት ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ሁልጊዜ አንድ እርምጃ ወደፊት ቀድሞ ከሚገኘው የግራ ክንፍ ኃይል ጋር ለመስተካከልና ብሎም የግራ ክንፉን ለማለፍ የነበረው ትግልና ጥረት ቀላል አልነበረም፤ ጥረቱም ተሳክቶ በሚያዝያ 1968 ዓ.ም ደርግ የመጨረሻውን ርዕዮተ ዓለማዊ እመርታ በማድረግ፣ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን በመመሪያነት አወጀ። በዚህ ድርጊቱም እየቀደመ ሲያስቸግረው ከነበረው የግራ ክንፍ የፖለቲካ ቡድን ጋር ተስተካከለ ማለት ይቻላል። ከዚያ የሚቀጥለው እርምጃ ራሱን የሠፊውንና የጭቁኑን ሕዝብ ትግል በግንባር ቀደምነት ለመምራት በታሪክ የታጨ ብቸኛ የፖለቲካ ኃይል አድርጎ ማየቱ ነው፡፡

ይህን አስደናቂ የደርግ የርዕዮተ ዓለም ጉዞ ካሰመረለት አንዱ፤ የግራ ክንፉ ተከፋፍሎ ወደ አብዮቱ መድረክ መውጣት ነው። በተለይም ከሀገር ውጭ የሚገኘው የተማሪው ንቅናቄ አካል አብዮቱ ሲፈነዳ በሁለት አክራሪ ጎራዎች ተሰልፎ ነበር። ኋላ ገሀድ እንደ ወጣው እነዚህ ሁለት ጎራዎች የኢሕአፓና የመኢሶን ድርጅቶች ተከታዮች ነበሩ። እነዚህ ሁለት አንጋፋ የግራ ክንፍ ኅቡዕ ድርጅቶች በተማሪ ድርጅቶች ሽፋን ደጋፊዎቻቸውን ማብዛትና ማጠናከር ተያይዘው ነበር። በአብዮቱ ዋዜማ ሁለቱ ጎራዎች በዓለም አቀፉ የተማሪዎች ድርጅት አወቃቀር ላይ ሳንጃ ቀረሽ ክርክር እያደረጉ ነበር። የኢሕአፓ ወገኖች በአዲስ መልክ የተዋቀረውን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን ሲደግፉ፣ የመኢሶን ተከታዮች ደግሞ በቁጥጥራቸው ስር የነበረው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እንዲቀጥል ይሟገቱ ነበር።

በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ያለው ደርግ ‹‹ሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ›› ዘመቻውን በተለያዩ ዘርፎች ማጧጧፍ ቀጥሏል፡፡

እንዲህ እንዲህ እያሉ ነጭና ቀይ ሽብር የሚባሉ የሽብር ድርጊቶች ተፈጥረው የደርግን ታሪክ የጦርነት ታሪክ አደረጉት። በመጨረሻም ደርግ በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይና አጋሮቹ በመሰረቱት ኢህአዴግ ተወግዶ መሪው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከሀገር ተሰደዱ። እነሆ የየካቲት አብዮትም የዚያ ታሪክ አካል ሆነ።

ጆሮ ገብ የታሪክ ክስተት የማያጣው የየካቲት ወር ከ6 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 8 ቀን 2010 ዓ.ም ደግሞ አሁን ላለው ለውጥ ምክንያት የሆኑት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሥልጣን ለቀቁ። የካቲት 8 ቀን 2010 ዓ.ም የተነገረው ሰበር ዜና የብዙዎችን ቀልብ ስቧል። ቀጥሎ ምን ይፈጠራል፣ ማን ይሆናል ሲባል ቆይቶ፤ በዚሁ በየካቲት ወር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኦህዴድ ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ። ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ሊሆን እንደሚችል ሰፊ ግምት ማግኘት ተቻለ። በኋላም በመጋቢት ወር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጠቅላይ ሚኒስትር መሆናቸው ይፋ ሆነ።

የየካቲት ወር እነሆ ከጥንት እስከ ዛሬ የታሪክና ፖለቲካ ክስተቶች ወር ሆኖ ይታወሳል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## የዙፋኑ አልጋ አዳሽ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

እልፍ የዘመን ፍርግርጎችን በመርገጥ ወደ ኋላኛው ዘመን የታሪክ ቋት ስናመራ ዘመን እንደ ቀልድ ያለፋቸው አንድ ሰው እናገኛለን፤ አለቃ ገብረ ሀናን። በአብዛኛዎቻችን የልጅነት ትዝታዎች ውስጥ የአለቃ ገብረ ሀና ቀልድ አይጠፋም።

አሉ፤ እያልን የምናወራቸው እልፍ ነገሮች ነበሩ። በእውንም አለቃ ገብረ ሀና የሚባሉ ሰው ነበሩ? ገሚሱ ነበሩ፤ ገሚሱ ደግሞ አፈ-ታሪክ እንጂ በጭራሽ አልነበሩም እያለ ሽንጡን ገትሮ ይሞግታል። የምናስታውሳቸው በቀልዳቸው ብቻ ሆነ እንጂ መኖርስ ነበሩ። እውነተኛው የሕይወት ማድጋቸውን ብንከፍት የያዘው ብዙ ነው። ቤተ መንግሥቱ ያለሳቸው አይደምቅም ነበር። በዙፋኑ ላይ አልጋ ወራሽ ባይሆኑም፤ የአልጋው አዳሽ ሆነው በዚሁ ዙሪያ ያለውን ሰው በሙሉ ለማደስ ሲታትሩ ነበር።

የወላለቀውን ለመጠገን፤ የጎበጠውንም ለማቅናት የሚጠቀሙት ቅኔ ነበር። ከአንደበታቸው እውቀት እንደ ዥረት የሚፈስ ቢሆንም፤ በብዙው የሚታዩት ግን ደፍርሰው ነበር። ሊቅነታቸው በአንዲት ጉዳይ ብቻ ያረፈች አልነበረችም። ከመንፈሳዊውና አለማዊው፤ ከሰማዩም፤ ከምድሩም፤ ከእግዜሩም ከሰይጣኑም ብቻ የሚቀራቸው የለም።

አለቃ ነገሮችን የሚያዩበትም ሆነ የሚስሉበት መንገድ ፍጹም የተለየ ነበር። ብልሀት፤ እውቀትና አስተሳሰባቸው ከቀልደኝነታቸው ጋር ተጣምረው በብዙ ነገሮች ከማኅበረሰቡ ያፈነገጡ አደረጋቸው። ተቀባይ አጡ እንጂ የሚሰጡትስ ብዙ ነበር። የማያደርጋቸው ነገርም አልነበረም። ሲያሻቸው ባለቅኔ፤ ሲያሻቸው ፈላስፋ፤ የሕግ ሊቅ፤ የድጓ ዝማሜው አስተማሪ፤ አስታራቂ የሀገር ሽማግሌ፤ ኮሚክ፤ ቁጡ፤ አስቂኝ፣ አናዳጅ፤ ብቻ ማርም እሬትም ነበሩ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ፤ አለቃ ገብረ ሀናን ሲገልጹ፤ "አለቃ ገብረሀና እጅግ የተማሩ የጎንደር ሊቅ ነበሩ። በዚህም ላይ ጨዋታና ኃይለ ቃልን ያውቁ ነበር" ሲሉ፤ የደራሲ መንግስቱ ለማ አባት፤ አለቃ ለማ ኃይሉ ደግሞ "የሙያ መጨረሻ እሳቸው አይደሉም ወይ? የሐዲስ መምህር ናቸው። የፍትሐ ነገሥት መምህር ናቸው። ... ሁሉን ስለሚያውቁ ደፍሮ እሳቸው ፊት የሚቆም አነበረም" በማለት ይገልፆቸዋል፡፡

የአለቃ ገብረ ሀና የሕይወት ታሪክ፤ የመነሻ ህብለ ሰረሰሩን ስንመዝ፤ ወደ ደቡብ ጎንደር ዞን፣ ፎገራ ወረዳ ይወስደናል። በ1814 ዓ.ም የወረታው ደስታ ተገኝ እና ወይዘሮ መልካሜ ይልማ እኚህን ለሰው ሁሉ ቅኔ የሆኑትን አለቃ ገብረ ሀናን ወለዱ። ገና ከልጅነታቸው የመናገርና ነገሮችን በፍጥነት የመረዳት ችሎታቸው እጅግ ከፍተኛ ነበር።

በዚያው በትንሽ ዕድሜ ከተወለዱበት አካባቢ ከፊደላት ጋር ተዋወቁ። የግእዝን ፊደላት እንደ ሸንብራ እየጠረጠሩ በማወቅ እስከ ማብጠርጠር ደረሱ። ከዚህን በኋላ እንግዲህ ከአእምሮ እየወጣ በአፍ የሚንቦገቦገውን የልጃቸውን የእውቀት ነበልባል የተመለከቱት ደስታ ተገኝ እንቦቀቅላውን ልጅ ይዘው ወደ ጎንደር ተሻገሩ። ከጎንደር የቄስ ትምህርት ቤት ገብተውም ዳዊቱንም፤ ድጓውንም፤ ዜማና አቋቋሙንም ከቅኔ ጋር አዋህደው ማጉት።

አለቃ የእውቀት እንጎቻ ቆርሰው እንደበሉ 26 ዓመት ዕድሜ ላይ ደረሱ። በሊቀ ካህንነት ተሹመውም ሰባት ዓመታትን በዚሁ ሲያገለግሉ ቆዩ። ሊቅነትና ነገር አዋቂነታቸው ባየ፤ በሰማቸው ዘንድ ሁሉ ጎልቶ መውጣት ጀመረ። ፍትሐ ነገሥትን ከስር መሰረቱ መርምሮ በማወቅ፤ በወቅቱ አለቃን የሚስተካከል አንድም አልነበረም።

በዚህም ምክንያት በዳኝነት ሸንጎ ላይ ተሰይመው ፍርድ ሰጪ፤ ፍትህ አምጪ፣ እንዲሆኑ ተደረገ። ከችሎት ወንበሩ ላይ ወጡ። የዚህን ጊዜ ነበር አለቃ ቀልደኛና ባለቅኔ ተረበኛ መሆናቸው የታወቀው። በነገር ወጋ ወጋ እያደረጉ፤ ብዙ እንዳይደማ በቅኔ እያሻሹ በማከም ከስህተትና ህጸጹ እንዲመልስ "ቢገባህ" ሲሉ ይነግሩታል። የገባውም፣ ያልገባውም በሳቅ ሲያውካካ፤ የተነካው ደግሞ መፈራገጥ ይጀምራል፡፡

ሸንጎ ላይ ሕዝብ ሰብስበው፤ ከሳሽና ተከሳሽ ችሎት አቁመው ሌባውን ሌባ፤ ቀማኛውን ቀማኛ እቅጭ






እቅጩን እየነገሩ ልክ ያስገቡታል። ሰዎች በአለቃ ቀልድ፤ ለየስህተታቸው የሽሙጥ መርፌ መወጋቱ ቢሰለቻቸው ጊዜ፤ "ተው እንጂ፣ እርሶ ትልቅ ሰው አይደሉም" በማለት መክረው ቢያስመክሯቸውም የሚሰሙ አልሆኑም፡፡

ጠሊቅነታቸው፤ በተለይ በሁለት ነገሥታት ዘመን፤ አንዱ ሔዶ ሌላው ሲመጣ አለቃ ከቤተ መንግሥቱ ቁጭ እንዳሉ አሉ። አልጋ ወራሽ ባይሆኑም፤ በግብራቸው አልጋ አዳሽ፤ ጥበብ አጉራሽ ናቸውና "ኖር!" በማለት፤ የሚመጣውን እየተቀበሉ ፊት ኋላ፤ ግራ ቀኙን ያጤኑታል። የቤተ መንግሥቱ መውጫና መግቢያም ቢሆን፤ ነገሥታቱ እንኳን እንደሳቸው አያውቁትም። የቀራቸው ነገር ቢኖር ዙፋኑና አጼ የሚለው የንግሥና ማዕረግ ብቻ ነው። በዚህ ጥልቅ እውቀትና በነገር አዋቂነታቸው በነገሥታቱ ዘንድ ተፈላጊ ቢያደርጋቸውም፤ ነገር ግን ያዩትን ስህተት ሁሉ ካላረምኳችሁ ማለታቸው ምቾትን የሚሰጥ አልነበረም። ወዳጅነታቸው እንዳይቀጥልም እንቅፋት ሆኗል። የተበላሸ ነገር በተመለከቱ ቁጥር የቅኔ ዱላ እያወረዱ፤ በአፍጢም ስለሚደፉ፤ ጠቢብነታቸው ትክክለኛውን ስፍራ ለማግኘት አልቻለም።

ቅሉ ምን ሞገደኛ መምህር ቢሆኑም፤ በቤተ መንግሥት በኩል ከመፈለግ አላገዳቸውም። የትንሹ ዓሊ አጫዋችና የእውቀት አባት ሆኑ። እየኮረኮሩ ማሳቁንም ሆነ ማደስ መስራቱን እንደሆን ተክነውበታል። ከቤተ መንግሥቱ መንደርም ዝናቸው እየናኘ መምጣት ጀመረ። በዚህ መሀል አጼ ቴዎድሮስ የንግሥና ዘውዳቸውን ጭነው ወደ ዙፋኑ መጡ። እየዋሉ እያደሩ አለቃን ቢያዩዋቸው ጊዜ፤ ፈገግም ቆጣም ያሰኟቸው ጀመር።

የቤተ መንግሥቱን ሰዎች በነገር ሸንቆጥ እያደረጉ አሳራቸውን እያበሉ አስቸገሩ። በዚህም የተነሳ ወደ ንጉሡ የማይመጣ ስሞታና አቤቱታ አልነበረም። ከአጠገባቸው ዞር አድርገው ያን ድንቅ እውቀትና ችሎታቸውን ለማጣት አልፈለጉምና እንደ ጸሀይም እንደ ደመናም የሆነውን የአለቃን ባህሪ ቻል አድርገው ቆዩ። አለቃም ፍትሐ ነገሥትን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉመው ጻፉ። በዚህም የመጀመሪያው ሰው ነበሩ።

ከዕለታት በአንዱ ቀን አጼ ቴዎድሮስ አለቃን አስጠሯቸው። አለቃም እጅ ነስተው ከፊት ቆሙ። "ገብረ ሀና" አሉ አጼ ቴዎድሮስ። "አቤት ጌታዬ!" "ገብረ ሐና ፍትሐ ነገሥቱን ጻፍ፤ ፍርድ ስጥ .. ገንዘብ ያውልህ፤ ቀልድህን ግን ተወኝ!" አሉ፤ በትዕዛዝም በተማጽኖም። የአለቃ ባህሪ ግን የማይፋቅ፣ የማይፈቀፈቅ ሆነና እንኳንስ ሊያቆሙ ይበልጥ ባሰባቸው።

በቤተ መንግሥቱ ስር ካሉት ሁሉ አለቃ በነገረ ቅኔ አንካሴ እየወጉ የሚያስጨንቁት ብላታ አድጎ የተባለ የንጉሡ ባለሟል ነበር። ስሙን እያነሱ፤ "አድግ ማለት በግዕዝ አህያ ማለት ነው" ይሉታል። አድጎ፤ በየጊዜው የሚሰነዙርበትን ትችት እየወሰደ ለንጉሡ ቢዘረግፍላቸው ጊዜ፤ መሸከም ሰለቻቸውና "በሉ አሁንስ በምላስ ሳይሆን ታገሉና በጉልበት ተፈታተሹ" በማለት መለሱላቸው። ሁለቱም ወደ ትግሉ ሜዳ ገቡ።

አለቃ የምላስ እንጂ የጉልበቱ ጡንቻ ነገር አልሆንልህ አላቸውና ተሸነፉ። "ታዲያ አሁንስ ምን ይውጥህ" አሏቸው አጼ ቴዎድሮስ፣ አለቃን። "ድሮስ ቢሆን ትግል የአህያ አይደል" አሉ አለቃም። አጼ ቴዎድሮስ ቤተ ክርስቲያን አንጸው ነበርና አለቃን ጠርተው "እንዴት አየኸው?" በማለት፤ "ይህ ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ነው ወይንስ ጠባብ?" ይሏቸዋል፤ አለቃም "ኧረ! ሰፊ ነው እንጂ፤ ምን ጎድሎት? ለሁለት ቀሳውስትና ለሦስት ዲያቆናት ይበቃል" ሲሉ መለሱ፡፡

በጊዜው ለአንዲት ደብር ሁለት ቄስና ሦስት ዲያቆን ይበቃል፤ በማለት የወሰኑትን ውሳኔ፤ አለቃ በነገር ሸንቆጥ እያደረጓቸው ስለመሆኑ፤ አጼ ቴዎድሮስ ገባቸው።

ከዛ ወዲያ፤ አጼ ቴዎድሮስ ብዙ ጉዳዮችን አውጥተውና አውርደው ይበጃል በማለት አለቃ ገብረ ሀናን ለጨለቆት ሥላሴ አለቃ አድርገው በመሾም ወደ ትግራይ ላኳቸው። እንግዲህ ከነገሩ ጾም ይደሩ ማለታቸው ነው። አለቃም በዚያው በትግራይ ሲያገለግሉ ቆይተው በአንድ ወቅት ካህናት በንጉሡ ላይ ባስነሱት አመጽ ቀንደኛው ተሳታፊ ሆነው ተገኙ።

የዚህን ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ የአለቃ ነገር ቆረጠላቸው። አልጋ አዳሽ ሳይሆን አልጋ አፍራሽ መስለው ታዩአቸው። በጣም ተቆጥተውም ዛቱ። አለቃም ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርሀት ገባቸው። አጼ ቴዎድሮስ ማምረራቸውን ስላወቁ፤ ሸሽተው ጣና ሐይቅ፣ ሬማ መድኃኒዓለም ገዳም ገቡ። በዚህ ገዳም ሳሉ ከፈጣሪያቸው ብቻም ሳይሆን፤ ከራሳቸው ጋርም የሚነጋገሩበትን የጥሞና ጊዜ በማግኘታቸው፤ ያላቸውን ሁለ-ገብ እውቀት በመጠቀም በርካታ ነገሮችን ለመፍጠር ችለዋል።

በተለይም ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ "የተክሌ አቋቋም" እየተባለ ዛሬም ድረስ በብዛት በጎንደርና ጎጃም አካባቢዎች የሚጠቀሙትን ዝማሜ በዚህ ጊዜ ነበር ያዘጋጁት። ተክሌ የአለቃ ገብረሀና የበኩር ልጃቸው ነበር። የዝማሜውን ሀሳብ ያገኙትም ድንገት ሸንበቆ በንፋስ ሲወዛወዝ ተመልክተው ነበር።

በ1864 ዓ.ም አጼ ቴዎድሮስ ሲሞቱ፤ አጼ ዮሐንስ በትግራይ መንገሣቸውን ሰሙና ከገዳሙ ወጥተው ተመልሰው ወደ ትግራይ አመሩ። ቤተ መንግሥት የለመዱ ናቸውና፤ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ግንኙነት ስለመፍጠራቸው ግን በውል አይታወቅም። የኋላ፣ እንደገና ሌላ ነገር ሰሙ፤ አጼ ምኒልክ በሸዋ ነግሠዋል የሚል። ይሄኔ፤ በሉ ደህና ሁኑ ሲሉ፤ እንደገና ወደ ሸዋ ገሰገሱ።

የሸዋው ምኒልክና አለቃ ገብረ ሀና መልካም ግንኙነት ፈጠሩ። አጼ ምኒልክ ትንሽ ልጅ ሳሉ አለቃን በአጼ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ውስጥ ያውቋቸው ነበር። ልጅ ሆኖ አለቃን የሚወድ እንጂ የሚጠላ አልነበረምና በዚያው የልጅነት ትውስታ እጃቸውን ዘርግተው በደስታ ተቀበሏቸው። መቀበል ብቻም አይደለም፤ በደቡብ ጎንደር በሚገኘው በአቡነ ሐራን ገዳም ላይ ሾሟቸው። ታዲያ በአንድ ወቅት አካባቢው በከባድ ረሀብና ድርቅ ተመታ፡፡

አለቃ ያ ውልፍ የሚያደርጋቸው የቸርነት ውቃቢያቸው ተነሳና ከገዳሙ ገንዘብ ላይ አንድ ሺህ ብር አውጥተው እየዞሩ ለገበሬው አከፋፈሉት። በዚህ ምክንያትም ወንጀል ሠርተዋል በማለት፤ ለፍርድ ወደ አዲስ አበባ አመጧቸው። በወቅቱ የፍርድ ሚኒስትር የነበሩት አፈ ንጉሥ ነሲቡ "አለቃ ስህተት ሠርተዋል" በማለት ፈረዱባቸው።

በመሃል ወሬው አጼ ምኒልክ ጋር ደረሰ። ጉዳዩ በሰበር ወደ ዙፋን ችሎቱ ተሸጋገረና በንጉሡ ፊት ቆሙ። "ምንድን ያጠፋኸው?" ቢሏቸው፤ ያደረጉትን አስረዱ። አጼ ምኒልክም፤ "ይሄማ የሚያሸልም እንጂ የሚያስከስስ አይደለም" በማለት ነጻ አወጧቸው። በእንጦጦ ማርያም ገዳምም አለቃ አድርገው እንደገና ሾሟቸው።

ከዕለታት በአንዱ ቀን በዚያው ደብር የሚያገለግል አንድ መልከ ጥፉ ደብተራ አለቃ በባዶ እግራቸው ሲራመዱ ተመለከተና "መምህር ምነው በባዶ እግርዎ ጫማ አይገዙም?" ቢላቸው፤ "እስቲ አንተ ፊት ግዛ እኛ ደግሞ ኋላ እንገዛለን" በማለት፤ የጥያቄውን መልስ በዱላ አስታቀፉት። ከዛ ወዲያ አለቃ ወደ ጎንደር ተመልሰው፣ የነበራቸውን ተባእታዊ ክብረ ንጽህና አፍርሰው ቆንጆዋን ልጃገረድ - ማዘንጊያን አገቡ። ስንቱን ችለው አልፈውት እንጂ፣ ዝነኛና የቤተ መንግሥቱ አውራሽ፣ አጉራሽ ከመሆናቸው የተነሳ አለቃን የሚፈልጉ ሴቶች ጥቂት አልነበሩም።

አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት ከሆነ፤ እንዲያውም ይሻሙባቸው ነበር። ከማዘንጊያ ጋር ውሀ ተጣጥተው ጎጆ ከቀለሱ ኋላ ተክሌ የተባለውን ወንድና በፍታ የተባለችውን ሴት ልጅ ወልደው፣ ከብረው፣ ሠላሳ ጥጆችንም አስረው ኖረዋል። የተክሌ አቋቋም የተሰኘውንም ዝማሜያቸውን፤ ለወንድ ልጃቸው በግል እያስተማሩት ኋላም እንደ አባቱ ሊቅ ሆኖ በስሙ የተሰየመውን የአባቱን ዝማሜ አበረከተ። በአንድ አጋጣሚ፤ ተክሌ ዝማሜውን በተመስጦ ሲያቀርብ ተመልክተው የወደዱት የወሎው ንጉሥ ሚካኤል በስሙ እንዲሰየም አደረጉ።

አለቃ ይሉኝታና ውለታ የሚያስራቸው ሰው አልነበሩም። ነገሮችን የሚመለከቱበት መነጽር ከብዙኀኑ የተለየ ነበር። አንዳች የማይመስል ነገር ከተመለከቱ ከማረም ወደ ኋላ አይሉም። ያደረገልኝ ሰው ነው ብለው በይሉኝታ እራሳቸውን አይጠፍሩም። በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከመሳፍንቱና መኳንንቱ ጋር ቁጭ ብለው ሲጨዋወቱ እንኳን ያልጣማቸውን በቅኔና በቀልድ አስደግፈው ይሸርቡታል። ይህ ነገር ከብዙዎቹ ጋር ያጎረብጣቸው ያዘ።

በአድዋ ጦርነት ወቅት ታላቅ ጀብዱ ፈጽመው ለነበሩት ለደጃዝማች ባልቻ ሳፎ ምኒልክ የሚወዱትን ጎራዴ አንስተው ሸለሟቸው። ይህን ጊዜ ታዲያ "ወይ ጎራዴ፣ ወይ ጎራዴ ከቤቷ ገባች ..." ሲሉ በሽሙጥ በመናገራቸው፤ ባልቻም ካልገደልኩት ብለው ተነሡ። በዚህ ሳያበቃ ከእቴጌ ጣይቱ ጋርም በሌላ ነገር ኩርፊያ ውስጥ ገቡ። ሰበብ ሲፈልግ የከረመው መላው የቤተ መንግሥት ሰው አጋጣሚዋን በመጠቀም አደሙባቸው።

አጼ ምኒልክም፤ አለቃን አብዝተው ቢወዷቸውም የማይነኩትን ሁለት አይኖቻቸውን ነክተዋልና ቅር ተሰኙባቸው። አዲስ አበባን እንዲለቁም ተወሰነባቸው። በጎንደር የተወሰነ ከቆዩ በኋላ ልጃቸው ተክሌን ጠርተው አለቃ ገብረ ሀና ሞተዋል ብለህ ተናገር በማለት ወደ አዲስ አበባ ሰደዱት። መርዶው ሲሰማ ሁሉም ቅሬታውን እረስቶ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ሀዘን ሆነ፡፡

ከዚያው ሆነው እርማቸውን ካወጡ ከጥቂት ቀናት በኋላም አለቃ ገብረ ሀና አዲስ አበባ መጥተው "እንደምን ከረማችሁ?" በማለት ከቤተ መንግሥቱ ዘው ብለው ገቡ። አገር ምድሩ ጉድ! አለ። አጼ ምኒልክም "ሞቱ ከተባሉ በኋላ ከየት ነው የመጡት?" ቢሏቸው ጊዜ "በሰማይ ጣይቱ የለች፤ ምኒልክ የለ፤ ጠጅ የለ፤ ጮማ የለ፤ ባዶ ቤት ቢሆንብኝ ለጠባቂው ጉቦ ሰጥቼ መጣሁ" ሲሉ አሳቋቸውና የተኳረፏቸውን ሁሉ ይቅር አስባሏቸው፡፡

የመጨረሻው ስንብት፤ አልጋ አዳሹ፤ የቤተ መንግሥቱ ሊቅ ጠሊቅ፤ አለቃ ገብረ ሀና ፍትሐዊ አይደለም ባሉት በአንድ ጉዳይ ላይ ከአጼ ምኒልክ ጋር የከረረ ሙግት ውስጥ ገቡ። በዚህ ምክንያትም ፍቅራቸው ዳግም ሻከረና ጠቅልለው ወደ ቀያቸው ተመለሱ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አለቃ ሌላ ሰው፤ ሌላ ማንነት ያዙ። እንደ ቀድሞው መሳቅና ማሳቅ፤ ከእውቀት ባህር እየጨለፉ ማጠጣት ቀርቶ ለመናገር እንኳን አልፈለጉም። ዝምታን መረጡ።

"ምን ሆኑ?" ቢባሉ ምላሽ እንኳ አይሰጡም። አፋቸው የሚከፈተው ለምግብና ውሀ ብቻ ሆነ። ከጥሩ ምግብም ሆነ ከጥሩ መጠጥ ተቆጠቡ። ብዙ መጻሕፍትን በዙሪያቸው ሰብስበው ከፈጣሪያቸውና ከመጻሕፍቱ ጋር ብቻ በንስሀ ያወራሉ። እድሜያቸውም በጣም ገፋ፤ እርጅናም ተጫጫናቸው፤ በመጨረሻም ዝም ብለው ዝም እንዳሉ 1984 ዓ.ም አረፉ፡፡

# ዓለም አቀፍ



አብዲብካ ከባክሙት በመቀጠል ለሩሲያ ትልቅ ስትራቴጂካዊ ፋይዳ ያላት ከተማ መሆኗ ተገልጿል

## የትጥቅ እጥረት ያጋጠማት ዩክሬን ወታደሮቿን ከአብዲብካ ከተማ አስወጣች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የዩክሬን ወታደሮች ከአብዲብካ ከተማ ሙሉ በሙሉ ለቀው እንዲወጡ መደረጉ ተገለጸ።

የሀገሪቱ ጦር አዛዥ አሌክሳንደር ሲርይስኪ በሩሲያ ጦር ከበባ ውስጥ ከመግባት ለመዳን ውሳኔውን ማሳለፋቸውን ተናግረዋል።

በምሥራቃዊቷ የዩክሬን ከተማ ላለፉት አራት ወራት በተካሄደ ጦርነት ዩክሬን ከፍተኛ ጉዳት ማስተናገዷ የተነገረ ሲሆን፥ ሞስኮ በጦር መሣሪያም ሆነ በወታደሮች ብዛት ብልጫውን መያዟም ተመላክቷል።

በሩሲያ ወደተያዘችው ዶኔስክ መግቢያ በር የሆነችው አብዲብካ ለወራት በተካሄደው ጦርነት ፈራርሳለች፤ ከ34 ሺህ በላይ ሰዎች መኖሪያ በነበረችው ከተማ አሁን 1 ሺህ ገደማ ሰዎች ይኖሩባታል ተብሏል።

ከባክሙት በመቀጠል ለሩሲያ ከፍተኛ ስትራቴጂካዊ ፋይዳ እንዳላት የተነገረላት ከተማ በሞስኮ ወታደሮች መያዟ ከተነገረ ቢቆይም ፕሬዚዳንት ዜለንስኪ ከተማ ድረስ በመዝለቅ አልተያዘችም ሲሉ ማስተባበላቸው ይታወሳል።

«ወታደሮቻችን የሩሲያን ጦር ለማውደም የሚችሉትን ሁሉ አድርገው ከፍተኛ ኪሳራ አድርሰዋል» ያሉት አዲሱ የዩክሬን ጦር አዛዥ አሌክሳንደር ሲርይስኪ፥ ሩሲያ ድል እንዳደረገቻቸው በይፋ ባይገልጹም «ወታደሮቻችንን ከከበባ ለመታደግ ወጥተናል» ብለዋል።

የአሜሪካ የብሔራዊ ደህንነት ምክርቤት ቃል አቀባዩ ጆን ኪርቢ በበኩላቸው የዩክሬን ወታደሮች የትጥቅ ችግር ስለገጠማቸው ከአብዲብካ ከተማ ለቀው ለመውጣት መገደዳቸውን ነው የተናገሩት።

የአሜሪካ ሴኔት ባለፈው ሳምንት ለዩክሬን ያጸደቀው የ60 ቢሊዮን ዶላር በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤቱም ጸድቆ በፍጥነት ለኬቭ ሊደርስላት ይገባልም ብለዋል።

ዩክሬን ሁለተኛ አመቱን ከቀናት በኋላ በሚይዘው ጦርነት ከምዕራባውያን የምትጠባበቀው ድጋፍ በፍጥነት አለመድረሱ የመልሶ ማጥቃት ዘመቻዋን ወደኋላ እንዳስቀረው ገልጻለች።

የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ዋና ጸሐፊ የንስ ስቶልተንበርግም የአሜሪካ ድጋፍ መጓተት በአውደ ውጊያዎች ላይ ተጽዕኖውን እያሳረፈ እንደሚገኝ መናገራቸውን ፍራንስ 24 አስነብቧል።

የጀርመኑ ኬል ኢንስቲትዩት መረጃ እንደሚያሳየው አሜሪካ ከየካቲት 2022 እስከ ታኅሣሥ 2023 ለዩክሬን 45 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ አድርጋለች (በወር ሁለት ቢሊዮን ዩሮ ገደማ)።

የአውሮፓ ኅብረትና 27ቱ አባል ሀገራት ጦርነቱ እንደጀተመረ 49 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዩሮ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸው፤ እስካሁን 35 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዩሮ የሚያወጣ ወታደራዊ ድጋፍ አድርገዋል።

ይህ ሁሉ ድጋፍ በጦርነቱ ላይ የሩሲያን ግስጋሴ ከመግታት ውጪ የተያዙባትን ስፍራዎች ማስለቀቅ ያላስቻላት ኬቭ ተማጽኖዋን ቀጥላለች፤ ፕሬዚዳንት ዜለንስኪም ወደ ጀርመን አቅንተዋል።

## “የአፍሪካ ሀገራት በቡድን 20 ውስጥ በአባልነት መካተት አለባቸው”

- ሉላ ዳሲልቫ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በርከት ያሉ የአፍሪካ ሀገራት በቡድን 20 ውስጥ በአባልነት መካተት አለባቸው ሲሉ የብራዚል ፕሬዚዳንት ሉላ ዳሲልቫ ጥሪ አቀረቡ።

37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ስብሰባ በአዲስ አበባ በመካሄድ ላይ ነው። በስብሰባው ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የብራዚል ፕሬዚዳንት ሉላ ዳሲልቫ፣ ያለ አፍሪካ ዓለም ምንም ነች ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ የአፍሪካ ኅብረት የቡድን 20 አባል መሆኑን እንደሚደግፉት አስታውቀዋል።

ይህ ብቻ በቂ አይደለም ያሉት ፕሬዚዳንት ሉላ ዳሲልቫ፣ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም የቡድኑ ቋሚ አባል መሆን እንዳለባቸው ጥሪ አቅርበዋል።

ብራዚል ከአፍሪካ ጋር ተቀራርባ መሥራት እንደምትፈልግም ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል።

አፍሪካ እና ብራዚል በመካከላቸው ያለውን የባሕር ድንበር እንደ ድንበር ሳይሆን እንደ ጸጋ በመቁጠር የበለጠ ሊቀራረቡ ይገባል ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

በመድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የፍልስጤም ጠቅላይ ሚኒስትር መሐመድ ሽታይህ ፍልስጤማውያን በእሥራኤል ምክንያት ከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ናቸው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው በርካታ ሀገራት ጦርነቱ እንዲቆም ጥሪ ያቀርባሉ፣ ነገር ግን ከጥሪ በዘለለ እርምጃ ያስፈልጋል ብለዋል።

የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ዛሬ ይጠናቀቃል። የዘንድሮው የኅብረቱ መሪዎች ጉባኤ ዋነኛ ትኩረቱን በትምህርት ልማት ላይ ያደርጋል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

# ስፖርት





## ሰማያዊው የዳኞች ካርድ!

ቦጋስ አበበ

በየትኛውም የእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ቢጫና ቀይ ካርዶች የተለመዱ ናቸው። ከ1970 የሜክሲኮ ዓለም ዋንጫ ጀምሮ የጨዋታ ዳኞች እነዚህን ሁለት ካርዶች ይዘው መመልከትም ለየትኛውም የእግር ኳስ ቤተሰብ አዲስ አይደለም። ከተለመዱት ሁለት አይነት ካርዶች በተጨማሪ ሶስተኛ የሆነውን ሰማያዊ ካርድ መመልከት ግን ለማንም ቢሆን እንግዳ ነው።

የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር ቦርድ (አይ. ኤፍ.ኤ.ቢ) ሰሞኑን በእግር ኳስ ጨዋታ ወቅት ዳኞች ሰማያዊ ካርድ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ፈቃድ ሰጥቷል። የእንግሊዝ የእግር ኳስ ማኅበርም ሰማያዊ ካርድ በ2024-25 የኤፍ.ኤ ዋንጫ ውድድር ላይ እንዲሞከር ፈቅዷል፡፡

ሰማያዊ ካርድ ሆን ብለው ጥፋት ለሚፈፅሙ ተጫዋቾች እንዲሁም በጨዋታው ዳኛ ውሳኔዎች ላይ ያልተገባ ምላሽ ለሚያሳዩ ተጫዋቾች የሚሰጥ መሆኑንም ተገልጿል።

ሰማያዊ ካርዱ ከቢጫ ካርድ ጋር ተመሳሳይ አቅም እንዳለው የተገለጸ ሲሆን፤ በጨዋታ መካከል ሁለት ሰማያዊ ካርድ የተመለከተ ተጫዋች እንደ ሁለት ቢጫ ካርድ ተቆጥሮ ከሜዳ እንዲወጣ ይደረጋል። ሰማያዊ ካርዱ ቢጫ እና ቀይ ካርድ ወደ አገልግሎት ከገቡበት ከ1970 ወዲህ ዳኞች የሚጠቀሙበት የመጀመሪያው አዲስ ካርድ እንደሚሆንም ተነግሯል። ሰማያዊ ካርድ የተመለከተ ተጫዋችም ለ10 ደቂቃ ያክል ከሜዳ ወጥቶ እንዲቆይ ከተደረገ በኋላ ተመልሶ ጨዋታውን እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው ተብሏል። አንድ ሰማያዊ እና አንድ ቢጫ ካርድ የተመለከተ ተጫዋችም በድምር ቀይ ካርድ ተሰጥቶ ከጨዋታ እንዲወጣ ይደረጋልም።

ይሁን እንጂ ይህ ነው የተባለ የሙከራ ጊዜ ያልተቆረጠለት ሲሆን፤ የእንግሊዝ የእግር ኳስ ማኅበር በ2024-25 የወንዶች እና የሴቶች ኤፍ.ኤ ዋንጫ ውድድር ላይ እንዲሞከር ፈቅዷል።

ፊፋ 'ሰማያዊ ካርድ' እየተባለ የሚጠራውን አዲሱን ካርድ ማጣራት እንደሚፈልግ እና የእግር ኳስ ደረጃ የተሳሳቱ እና ያለጊዜው የተከሰተ ነው ሲል አጣጥሎታል። ይህ ካርድ የሚሞከር ከሆነም በዝቅተኛ ደረጃ በሚገኙ የእግር ኳስ ጨዋታዎች ላይ የተገደበ መሆን እንደሚገባው እና ሙከራውም ኃላፊነት የተሞላበት ሊሆን እንደሚገባ አሳስቧል።

በእግር ኳስ ከቢጫና ቀይ ካርድ በተጨማሪ ሌላ ካርድ አገልግሎት ላይ የማዋል ጉዳይ ዛሬ የመጣ ነገር አይደለም። ሃሳቡ በዋናነት የተጠነሰሰው በቀድሞው ፈረንሳዊ ኮከብና የአውሮፓ እግር ኳስ ማኅበር ፕሬዚዳንት ሚሼል ፕላቲኒ ነው። ይህም 'sin bin' ወይም ተጫዋቾች የዳኛን ውሳኔ ተቃውመው ያልሆነ ቃል ሲሰነዝሩ ወይም ምልክት ሲያሳዩ እንዲሁም ዳኛ ሲንቁ ለጊዜያዊ ቅጣት (ለ10 ደቂቃ) የሚመዘዝባቸው ካርድ እንዲሆን የታሰበ ነው። ከዚህ ባሻገር ተጫዋቾች በጨዋታ ወቅት ስፖርታዊ ጨዋነትን እንዳይዘነጉ ለማስታወስና ስፖርታዊ ጨዋነትን ለማበረታታት ዳኞች እንዲመዙት በማሰብ ነው ሃሳቡ የመነጨው።

ይህ ሃሳብ ሲመነጭ ግን ከሰማያዊ ይልቅ ነጭ ካርድ ነበር የታሰበው። ሃሳብ እስካሁን በእግር ኳስ አልተስፋፋም ወይም ተግባራዊ አልሆነም። በፖርቱጋል ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ወደተግባር ለመለወጥ ጅምሮች ታይተዋል። በፖርቱጋል የሴቶች አምስተኛ ዲቪዚዮን የስፖርቲንግ ሊዝበንና ቤኔፊካ ጨዋታ ነጭ



ካርድን ተግባራዊ ለማድረግ የተሞከረ ሲሆን ተጫዋቾች ስፖርታዊ ጨዋነትን ሲያሳዩ ለማበረታታት ነበር ጥቅም ላይ የዋለው።

ነጭ ካርድ እንደቢጫና ቀይ ካርድ ሁሉ ወጥ የሆነ ሕግ ተደንግጎለት በዓለም አቀፍ ደረጃ በቅርቡ ተግባራዊ ሆነው ከሚተገበሩ አዳዲስ ጉዳዮች አንዱ እንደሚሆን ተነግሮ የነበረ ቢሆንም አሁን ሃሳቡ ወደ ሰማያዊ ካርድ የተለወጠ ይመስላል።




# ልጆች ከእረፍት መልስ

እዮሩስ ተስፋዬ

እንዴት ናችሁ ልጆችዬ? ሠላም ናችሁ? የአንደኛ ወሰነ ትምህርት (ሴሚስተር) ፈተና ወስዳችሁ ከጥቂት የእረፍት ቀናት በኋላ እንኳን ወደ ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ተመለሳችሁ እንበላችሁ አይደል? በጣም ጥሩ። ታዲያ ልጆችዬ ጓደኞቻችሁን፣ መምህራኖቻችሁን፤ እንዲሁም፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ስታገኟቸው ምን ተሰማችሁ? በጣም ደስ እንዳላችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ሰዎች እረፍታቸውን የተለያዩ ነገሮችን በመከወን እንደሚያሳልፉ ታውቃላችሁ። እና ልጆችዬ የእናንተስ እንዴት ነበር? ግማሾቻችሁ መጻሕፍትን በማንበብ (የትምህርት እና የተለያዩ መጻሕፍትን)፣ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት፣ ስዕል በመሳል፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫወት (በመለማመድ) ቤተሰብ በመጠየቅ፤ ከወላጆቻችሁ (አሳዳጊዎቻችሁ) ጋር በመዝናናት፣ በመጫወት በመረዳዳት፤ ብቻ በተለያዩ ነገሮች እንዳሳለፋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ልጆችዬ፣ የፈተና ውጤታችሁስ እንዴት ነው? በጣም ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ውጤት ያመጣችሁ ተማሪዎች እንደምትኖሩ እንገነዘባለን። ከፍተኛ ውጤት ያመጣችሁ ልጆች በጥንካሬያችሁ፤ እንዲሁም፣ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ያገዛችሁን መንገድ አጠናክራችሁ መቀጠል ይኖርባችኋል። ብትችሉ ደከም ያለ ውጤት ላመጡ ጓደኞቻችሁ ልምዳችሁን ብታካፍሉ መልካም ነው።

እዚህ ላይ፣ "ጥሩ ውጤት ያላመጣነውስ ምን እናድርግ?" የሚል ጥሩ ጥያቄ ልታነሱ እንደምትችሉ ተስፋ አደርጋለሁ። ለእናንተም የምንላችሁ አለን፡፡



ልጆችዬ፣ ምን ማድረግ አለባችሁ መሰላችሁ? በቅድሚያ የዓመቱን ትምህርት ለማጠናቀቅ ጥቂት ወራቶች እንዳሉ መገንዘብ ይኖርባችኋል። ‹‹በቃ አንደኛ ሴሚስተርን አላለፍኩም፡፡›› ብሎ ከማዘን እና ከመቆጨት ይልቅ አሁንም በርትቼ ጥሩ ውጤት ማምጣት እችላለሁ ብላችሁ ማሰብ፤ ከዛም ማጥናት እና በትኩረት ትምህርታችሁን መከታተል። ይሄንን ካደረጋችሁ፣ በቃ - ለሚቀጥለው 100 በ100 ውጤት የእናንተ ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ ልጆችዬ፣ ‹‹እኔ እኮ ትምህርት አይገባኝም፡፡›› በፍጹም እንዳትሉ እሺ። ምናልባት አንድ የሠራችሁት ወይም ልብ ያላላችሁት ስህተት ይኖራል እንጂ ትምህርት የማይገባችሁ ሆናችሁ አይደለም። እናም ድክመታችሁ የቱ ጋር እንደሆነ ራሳችሁን በሚገባ ፈትሹ። ያን ጊዜ የእናንተ ችግር ምን እንደሆነ እና ለምን ጥሩ ውጤት እንዳላመጣችሁ ትገነዘባላችሁ ማለት ነው። በተጨማሪም ለወላጆቻችሁ፣ ለታላላቆቻችሁ እና ለመምህራኖቻችሁ ድጋፍ እንዲያደርጉላችሁ ብትነግሯቸው መልካም ነው፡፡

ከዚህ በኋላም ቢሆን በትምህርት ቤት ውስጥ ያላችሁን ትርፍ ሰዓት በጨዋታ ብቻ ከማሳለፍ ይልቅ፤ ወደ ቤተ መጻሕፍት ሄዳችሁ በርትታችሁ ካጠናችሁ ውጤታችሁ የማይስተካከልበት ምንም ምክንያት የለም። ከዚህ ጎን ለጎን ከትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በማጥናት፣ በመረዳዳት እና ስለ እምትማሩት ትምህርትና ስላልገባችሁ ጉዳይ በመጠያየቅ ብታሳልፉ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ያግዛችኋል እሺ ልጆች።

ልጆችዬ ፈተና ስትቀበሉ የመጀመሪያ ሥራችሁን ራሳችሁን መመዘን እንደሆነ ከዚህ በፊት ተጨዋውተን ነበር አይደል? ከዚህ በኋላም ቢሆን የአጠናን ስልታችሁን ማወቅ፣ በክፍል ውስጥ የሚኖራችሁ ተሳትፎ፣ ለፈተና የምታደርጉት ዝግጅት እና ሌሎች ነገሮች ጥሩ ውጤት ለማምጣት፤ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ጥሩ ውጤት ላላመጣችሁ ተማሪዎችም እንድታሻሽሉ ያግዛችኋል፡፡

ልጆችዬ፣ ወላጆቻችሁ እቤት ውስጥም ሆነ በተለያዩ ድርጅቶች ተቀጥረው ሥራዎችን ይሠራሉ። እናንተ በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት እንድታመጡም በጣም ይደክማሉ። እንደውም አንዳንዶቹ ከተጣበበ እና ከተጨናነቀ ጊዜያቸው ላይ ቀንሰው፤ እንዲሁም ከሥራ ቦታቸው እረፍት በመውጣት እናንተን ለማስጠናት፣ ለማሳወቅ፤ እንዲሁም ከማዝናናት በተጨማሪም የእናንተ የነገ ሕይወታችሁ የሠመረ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት እያደረጉ እንደሆነ ታውቃላችሁ አይደል? "በሚገባ!!!" የሚል ምላሽ እንደምትሰጡኝ ምንም ጥርጥር የለኝም። እናንተስ እነሱን ለማስደሰት ምን እያደረጋችሁ ነው? ልጆችዬ ወላጆች ከእናንተ የሚፈልጉት ነገር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ጎበዝ ተማሪ፣ ውጤታማ ልጅ፣ ሀገሩን የሚያስጠራ እና ጥሩ ሰው መሆንን ብቻ ነው የሚፈልጉት። ይህንን አውቃችሁ በርትታችሁ ተማሩ፤ እሺ ልጆችዬ፡፡

ወላጆችም ብትሆኑ ልጆቻችሁ ጥሩ ውጤት ካላመጡ "ለምን?" ብላችሁ በጋራ ከልጆቻችሁ ጋር ተወያዩበት። ልጆቻችሁን በፍፁም ከሌሎች ልጆች ጋር አታወዳድሯቸው። አቅም፣ እውቀቱ፤ እንዲሁም ጊዜው ካላችሁ አስጠኗቸው። ጎበዝ ተማሪ ጓደኛ እንዲኖራቸው፣ በክፍል ውስጥ በንቃት እንዲከታተሉ፣ ያልገባቸውን ነገር ያለፍርሃት እንዲጠይቁ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች እንዲሆኑ፤ ከትምህርት ቤት መልስ ቤት ውስጥ በጥሩ እና በተረጋጋ መንፈስ እንዲያጠኑ ብሎም የቤት ሥራዎቻቸውን እንዲሠሩ በሚገባ ማገዝ ይኖርባችኋል፡፡

ልጆችዬ፣ ከዚህ ቀደም ስለ ፈተና ዝግጅታችሁ፣ እረፍታችሁን እንዴት መጠቀም ወይም ማሳለፍ እንዳለባችሁ፤ ዛሬ ደግሞ ከእረፍት መልስ ትምህርታችሁን እንዴት መማር እንዳለባችሁ እና ማሻሻል ያለባችሁን ነገሮች ጠቆምናችሁ አይደል? እናተም "ይጠቅመናል" የምትሏቸውን ሃሳቦች ወስዳችሁ በሚገባ እንደምትተገብሯቸው ተስፋ አደርጋለሁ።

በሉ እንግዲህ ልጆችዬ፣ ትምህርታችሁን በርትታችሁ አጥኑ፤ አንብቡ፤ ጨዋታ ቀንሱ። ልጆችዬ፣ ሳምንት በሌላ ርዕሰ ጉዳይ እንደምንገናኝ ተስፋ በማድረግ እና መልካም ነገሮችን ሁሉ ለእናንተ በመመኘት በዚሁ እንሰነባበታለን።